**ORIGINAL ARTICLE**

# Some aspect of a History of Religious Coexistence and Understanding in Gondar Province to 1991

***Ebrahim Damtew*[1] *& Assefa Balcha (Ph.D)*[2]**

## *Abstract*

*The objective of this study is to survey the history of coexistence and mutual understanding among the Christian- Muslim population of Gondar province, Ethiopia. The study employed qualitative method in collecting relevant historical sources. These sources could be categorized as primary and secondary. Finally, the collected sources transformed to evidence, crosschecked and triangulated for valid synthesis. Though not properly understood, yet not exhaustively studied and recorded, the history of Ethiopia is characterized by shared and overlapped identities. This was the result of continuous interaction and integration of in this case religious communities for a prolonged period in the past. Dynamic relations across religions lines have been facilitated through political, sociocultural and economic activities. Such interaction eventually assisted to create common values to govern the society without discrimination. The finding of this paper affirms the existence of various social and cultural values among the two major religious groups in the study area. The shared cultural and social institutions such as yätutlej, abä lij Mizénät,däbayet, mähaber, Equb, Idir and others enabled them to share their sorrows and happiness, together, as manifested in building churches and Mosques as well as celebrating holidays together. Hence, the study area has for long been developed such values that glued Muslims and Christians despite their religious difference. Mutual understanding among different religious groups is not something that happens overnight, but the result of prolonged interaction and integration. The study recommends that cultural practices have to be studied thoroughly and communicated to the concerned bodies to learn more so as to ensure mutual respect, peaceful coexistence and enduring interfaith harmony.*

**Keywords:** Ethiopia, Gondar. Culture, coxsistance, shared identities, Christianity, Isalm

## አጽኅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሃይማኖት አብሮነትና መተሳሰብ ታሪክን በቀድሞ ጎንደር ክፍለሀገር ምን ይመስል እንደነበር በወፍ በረር ማሳየት ነበር። ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ምንጮችን በመሰብሰብ፣ በመፈተሽና በማቀናጀት ትንተና ሰጥቷል። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየን በኅብር የበለጸገ አንድነቷን ነው። በታሪክ ሂደት እንደምንረዳው አንድ የኅብረተሰብ ክፍል በሃይማኖት ወይም በጎሣ ይለየኛል ከሚለው ወገኑ ጋር መተሳሰብን፣ መከባበርንና መሰል መልካም እሴቶችን

1 *Department of History and Heritage Management, College of Social Science and the Humanities, University of Gondar, Ethiopia. Email:* alyouebrahim@gmail.com or ebrahim.damtew@uog.edu.et

2 *Department of History and Heritage Management, College of Social Science and the Humanities, Wollo University Ethiopia. Email: anegwo@gmail.com*

***This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.***

DOI: https://dx.doi.org/10.4314/erjssh.v11i2.3

ባጭር ጊዜ ሊያመጣቸው የሚችላቸው ጉዳዮች አይደሉም። በረጅም ጊዜ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔሃብታዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መስተጋብር የሚመጡ ናቸው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በልዩነት ውስጥ የሚያዛምዱ የጋራ እሴቶች እየተፈጠሩ ኑሮን ሲያሳልጡ ከትውልድ ትውልድም ሲሸጋገሩ ይስተዋላሉ። ለምሳሌ፤ በጎንደር ክፍለሀገር በተለይ የሁለቱን እምነት የክርስትናንና የእስልምናን ተከታዮች አቀራርበው፣ አዛምደውና አስተሳስበው ልዩነታቸውን አክብረው የሚኖሩባቸው በርካታ የባህላዊና ማኅበራዊ ተቋማት አበልጅና መሰል እሴቶች ነበሯቸው። "ዝምድና"፣ መከባበር፣ አብሮ መኖር፣ መጠያየቅ፣ መተባበር፣ ሃይማኖታዊ ባዕላትን አብሮ ማክበር፣ አብሮ መብላት፣ መጠባበቅ፣ መተማመን፣ እድር፣ ፀሎት፣ እርግማን፣ ምርቃትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። አካባቢው እነዚህንና ሌሎች እሴቶችን የሚያጠቃልል በብዝኀነት ውስጥ አንድነትን የሚያስተምሩ በተግባር የታዩ ያኗኗር ዘይቤዎች እንደነበሩት ጥናቱ ይጠቁማል። የእምነት መተሳሰብ ከሃይማኖቶች አብሮ መኖር ባህል ጋር በእጅጉ እንደሚወራረስ መገንዘብ ይቻላል።

ቁልፍ ቃላት፤ ኢትዮጵያ፣ ጎንደር፣ ባህል፣ አብሮነት፣ ክርስትና እስልምና

## መግቢያ

## ፩.የሃይማኖት መተሳሰብና አብሮነት በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሰራሽ መንገድ የመጣ በጎብር የደመቀና የተዋሰበ የአንድነት ታሪክ ያለው ስለመሆኑ ብዙም የሚያመራምር ጉዳይ አይደለም። ፕሮፌሰር ጌታቸው እንደሚሉት "ታሪክ አንድ ያደረገው ሕዝብ ያላት ሀገር ነች" (ጌታቸው፣ 2013ዓ.ም፥ 366)። ከዘርፉ ምሁራን ምርምር እንደምንረዳው የረጅም ጊዜ አብሮ መኖር እነዚህን የመሰናሰል ውጤት የሆኑትን የጋራ እሴቶች እንደፈጠራቸው የሚያመላክተን ነው (Taddesse,1988:5-6; Bahru,2023)።

ሁለቱ የዓለም ሃይማኖቶች ክርስትናና እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ መጀመሪያ ከተሰበኩበት ጊዜና አካባበቢ እምብዛም ባራቀ ዘመን ነበር ለማለት ይቻላል (ጌታቸው፣ 2013 ዓ.ም፥ 336፣ Taddesse, 1988; Hussein, 2001)። ይህን አጋጣሚ የፈጠረው የሀገሪቱ መልካዓምድራዊ አቀማመጥ ሲሆን፣ ሁለቱም እምነቶች መጀመሪያ ከተሰበኩበት መካከለኛው ምስራቅ ጋር ቅርበት ያለው መሆኑና ከዚሁ አካባቢ ጋር የነበረው ታሪካዊ ግንኙት ስር የሰደደ ስለነበረም ጭምር ነው። የሁለቱም እምነቶች አገባብ በሰላማዊ መንገድ መሆኑም ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ነው ( Sergew, 1972; Trimingham,1956)።

በኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ውስጥ የሀገር በቀል እምነቶች ተጽዕኖ ቀላል ነበር ባይባልም የአይሁድ፣ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ተጽዕኖ በሀገሪቱ ባህል ላይ ከፍተኛ ነው (Haggai,2013:1-5; Trimingham,1956፥24-30)። በተለይ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ትሩፋት ደግሞ ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ ይገኛል። ለዚህ ዋናው ምክንያት ሁለቱ ሃይማኖቶች በበርካታ ኢትዮጵያውያን ተከታዮችን ይዘው ለዘመናት መኖራቸው ነው (Hussien, 1996; Haggai,2013; Eloi,2017 )። ይህም ሀገሪቱ የራሷ ሀገር በቀል ሃይማኖታዊ ሥልጣኔ እንዲኖራት አድርጓታል። ኤርምያስ ያጠናቀረው የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ሐሳብ "...ይህ መንፈሳዊ ሥልጣኔ ለዘመናት በተለይ ተጠብቆ ሊቆይ የቻለው ቤተክርስቲያናችን ለብዙ ምእት ዓመታት በልዩ ጥንቃቄ ባደራጀቻቸው ትልልቅ ገዳማትና አድባራት ውስጥ እስከዛሬ ድረስ በሚሰጠው ትምህርት ነው..." (ኤርምያስ፣ 2015ዓ.ም፥412-413)። ይነስም ይብዛም በእስልምናው እምነት ዘርፍም ቢሆን እንዲሁ ነው ለማት ያስደፍራል (Hussien, 2001; Solomon, 1994)።

በኢትዮጵያ የክርስቲያኖችንና የሙስሊሞችን ታሪክ በተለይ ከመከባበርና ፍትሐዊነት ጋር በተገናኘ ለዓለም ሕዝብ ሲወሳ የሚኖረው ክርስቲያኑ የሀገራችን ንጉሥ አርማህ የነብዩ መሐመድ ተከታዮችን መቀበሉና ማስተናገዱ ነው (Pankhurst,1996; Sergew,1972)። ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱት የእስልምና እምነት ተከታዮች በአሁኑ ዐረቢያ መካና አካባቢው በእምነታቸው ላይ ይደረግ የነበረውን ጫና ለማሳለፍ ነበር። ነብዩ መሐመድም ወደ ሌላ ጎረቤት ሀገር ለምሳሌ፤ ሮማም፣ ፋርስም፣ ቻይናም፣ ሕንድም አላኳቸውም፤ የላኳቸው ግን ወደ አክሱም ኢትዮጵያ ነበር። ኢትዮጵያም መጥተው በነጻነት በእምነታቸው ኑረዋል። በትውልድ ሀገራቸውም በሂደት የእስልምና ሃይማኖት ሲጠናና ሲቀና የተመለሱ እንደነበሩ ሁሉ ከኢትዮጵያ ምድርም የቀሩ አልጠፉም

(Hussien, 1996፤ 2001፤ ኤርምያስ፣ 2015ዓ.ም.)። ይህ የታሪክ አጋጣሚ እንደ ኢሉዋ ፍቄ አገላለጽ፤

| | |
|---|---|
| "....widely known in Islam but also present in the Christian world, the famous episodes of the ¨hadìth, recounting the exile of some of the first adherents of Islam who were persecuted in Mecca and found refuge in the Christian Kingdom of Abyssinia, serve to emphasize the possibility of harmony between the two religions..." (Éloi Ficque,2006:39) | [....ይህ የታሪክ ክስተት በስፋት በዓለም የታወቀ ሆኖ ይገኛል። በተለይ በሃዲስ (የነብዩ መሐመድ ተግባራትን የሚያትት) ስለመጀመሪያዎቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች ተመካ ወደ ኢትዮጵያ ምድር መሰደድና ቀድማ ክርስትናን የተቀበለችው ኢትዮጵያ እነዚህን ስደተኞች ያስተናገደችበት መንገድ ወደ ፊት በአካባበቢው አብሮ ተከባብሮ በመኖር ረገድ መሠረቱ የጠና እንዲሆን ተስፋ ያሳየ ነበር ብሎ መናገር ይቻላል...] ። |

ከላይ እንደተገለጸው የነብዩ መሐመድን ተከታዮች ኢትዮጵያ የተቀበለችበትና ያስተናገደችበት መንገድ ባብዛኛው የሃይማኖት ግንኙነት በተለይ አብሮነትና መተሳሰብ በዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ ሲነሳ በሁሉም አዕምሮ የሚመጣ ነው። ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያን ከፍትሕ፣ ሰብዓዊነትና ግብረገብነት ጋር ያላትን እሴት በማድነቅ ለተበደሉ ሰዎች መጽናኛ ሀገር መሆኗን እንደመሰከሩላት የውስጥም የውጭም ሀገር የዘርፉ ምሁራን በምርምራቸው መስክረዋል (Seregew, 1972; Trimingham, 1956; Hussien, 1996, Haggai,2013፡5)።

ኢትዮጵያ ለእስልማና ሃይማኖት ባደረገችው አስተዋጽኦ የተነሳ ቀስበቀስ ከዐረቢያ ምድር በተስፋፋው ኢስላማዊ መንግሥትና ግዛት በበጎ ዐይን እንድትታይ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይነገራል። ለዚህም የነብዩ የኑዛዜ ቃል አስተዋጽኦ እንደነበረው ብዙዎችን ያስማማል (Taddesse 1972; Hussien, 2001)። ይሁን እንጂ ቀስበቀስ ዐረቦች ኋላም ቱርኮች ግብፆች የመሳሰሉት በእስልምና ከተዋኋዱ በኋላ የኢትዮጵያን ጥቅም በየምክንያቱ አልተጋፉም ለማለት ግን ያስቸግራል (Taddesse (1972:31-32; Haggai, 2013)።

በኢትዮጵያም ምድር ሃይማኖቶቹ ሲስፋፉ በተለይ በመካከለኛው ዘመን በሚባለው የታሪክ ክፍል በደጋማው በክርስቲያናዊው ማዕከላዊ መንግሥትና በምሥራቅና ደቡብ ምስራቅ ኢስላማዊ ግዛቶች መካከል ሰላማዊና ግጭትን የያዘ ግንኙነት እንደነበረ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ። በሀገሪቱ ታሪክ የሥልጣን ጉዳይም ይሁን የምጣኔ ሀብት ሃይማኖትን ምክንያት አድርጎ ከፍተኛ የእርስ በእርስ ጦርነትና ጥፋት ሲነሳ የአሥራ ስድስተኛውና የአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመናት የሚታወሱ ናቸው። ሆኖም ግን አብዛኛው ዘመን በሁለቱም አማኝ ሕዝብ መካከል ተሰናስሎና ተደጋግፎ መኖር መርሕ እንደ ነበር በርካታ ጥናቶች አረጋግጠዋል (ኀይሌ፣ 2017; ኤርምያስ፣ 2015 ዓ.ም፥ 415፤ Taddesse, 1972፣ ውዱ 2004፣ Hussien 2001;Bahru, 2001)። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሀገራችንን የሃይማኖት ታሪክ ጥናት ስንመለከት በብዛት የሃይማኖት አብሮነትና ሌላም ይህን የመሰሉ ግንኙነቶች በጠቀስ ጠቀስ ካልሆነ እምብዛም እንደዋና አርዕስተ ጉዳይ ተወስደው የተጠኑበት አግባብ ትንሽ ይመስላል (ኀይሌ፣ 2017፤ Taddesse, 1972; Hussien, 2001)። በቅርቡ ውዱ ጣፈጠ፣ አሰፋ ባልቻ፣ እንዲሁም አህመድ ሐሰን ያሳተሟቸውን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል (ውዱ፣ 2004 ዓ.ም.; Assefa, 2019; Ahmed , 2017 )።

ከላይ እንደተገለጸው በኢትዮጵያ ታሪክ የሃይማኖቶችና የአማኞች ግንኙነት ጉዳይ በተለያየ ጊዜ እንደየዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በመነጬ ምክንያቶች እንቅፋቶች አልነበሩበትም ለማለት ያስቸግራል (Bahru, 2001; Hussien 2001)። በርካታ ጥፋቶችም ደርሰዋል። ግንኙቱም ሲታይ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሰላማዊንም ግጭትንም፣ እርስ በእርስ መጠራጠርንም ያስተናገደ ነበር (Ibid; Hussien,2006; Solomon, 1994; Hussien, 1996; ውዱ፣ 2004 ዓ.ም.)።

ሀጋይ (2013:3) በግልጽ እንዳሰፈሩት፤

| | |
|---|---|
| "..History has many facets and each observer is inclined to emphasize one aspect or another..." | [የታሪክ ጥናት የተለያዩ እይታዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡ ፡ ይህም እንደ አጥኚው ዓላማና ትኩረት ሊወሰን የሚችል ይሆናል...]። |

የዚህ ጥናትም ዓላማ የሃይማኖት አብሮነትና መተሳሰብ የሚለውን ጉዳይ በወፍ በረር ለይቶ በቀድሞ ጎንደር ክፍለሀገር የሚያይ ሲሆን፣ በሀገሪቱ የነበሩትን ሃይማኖትን ምክንያት ያደረጉ ወይም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችን ለመፈጸም ሲባል ሃይማኖትን ወደ ፊት በቶሎ በማምጣት ግጭትና ጥፋት ያስከተሉ የሚመስሉ ወይም በግልጽ ያደረጉ አለመግባባቶች ወይም የሁለቱንም ደምሮ አያይም፤ ምክንያቱም ጉዳዩ ሰፊ በመሆኑና ከዚህ መጣጥፍ ዓላማ ወሰን ውጭ ስለሆነ ነው።

ምንም እንኳን ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ሐሳብ በጥልቀትና በስፋት የተጠና ነው ባይባልም ቅሉ የዘርፉ ምሁራን በጥናቶቻቸው እንደሚያሳዩት በሰላሙ ጊዜ ከቤተመንግሥት እስከ ተራው ሕዝብ የነበረ መስተጋብር መገለጫዎቹ መተማመን፣ መከባበር፣ መተባበርና የመሳሰሉትን ባሕርያት ነበሩት (ጎይሌ፣ 2017፣ Taddesse, 1970: 197; Hussien, 2006; Taddesse, 1972; Donzel, 1986፣ ውዱ፣ 2004 ዓ.ም.፤ ጌታቸው፣2011 ዓ.ም፡ 21 ፤በተጨማሪ ጌታቸው ፣2012 ዓ.ም፡413-14 )። ይህንን መልካም ግንኙነት የውጭም ሁኑ የሀገር ወስጥም መረጃዎች በተለያየ ጊዜ ምስክርነት ሰጥተውበታል (Beckingham and Huntingford,1958፡190-195፤Abir, 2011)። እንደሌሎች ልዩነቶች ሁሉ የሃይማኖት ልዩነትን ማክበር ተፈጥሮአዊ የሚያደርገው ነገር ያለ ይመስላል። ይኸውም አንድ የሃይማኖት ተከታይ ኅብረተሰብ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማሟላት አይችልም። ሌሎች ያስፈልጉታል፤ እርሱም ለሌሎች ያስፈልጋል። ተደጋግፎ ተረዳድቶ መኖር የግድ ይለዋል ማለት ነው። ይህ በኅብረተሰብ እድገት የታየ እውነት ይመስላል (Bahru,2023)። ስለሆነም በልዩነት ውስጥ ለጋራ ጥቅምና ልማት ሲባል መቀራረብ፣ መተዋወቅ፣ መተሳሰብና መረዳዳት በተለያዩ ወገኖች መካከል እንደነበረ ወደፊትም እንደሚኖር ማስተዋል ይቻላል። ለምሳሌ፤ ንጉሡ ነጋዴዎቹን ይፈልጋቸዋል፤ ነጋዴዎቹም በሰላም ካሰቡት ደርሰው ይነግዱ ዘንድ ጥበቃ እንዲያደርጉላቸው ንጉሡንና ጭፍሮቻቸውን ይፈልጋሉ። ከሀገር ሰውነት በበለጠም የሙያ ጉዳይም ጭምር አቀራራቢ ነበር ለማለት ይቻላል። በተዋረድ እስከ ተራው ማኅበረሰብ ድረስ እንዲሁ ወዳጅነትና መጠቃቀም እንደነበረ መረዳት ይቻላል። የንግድ መስፋፋት፣ የከተሞች በንግድ መስመሮች አካባቢ መመሥረት፣ መዋዕለ ንዋይና የኑሮ መሻሻል ለንጉሡና በዙሪያው ላሉ ሰዎች የወታደሩ ክፍል፣ እንዲሁም ለሃይማኖት መሪዎች ለመላው ሕዝብ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህ የሕይወት አስገዳጅና የኑሮ ማሻሻያ መንገድ በኢትዮጵያ ብቻ የነበረ ሳይሆን በሌላው ዓለምም የሚስተዋል ጉዳይ ነው (Meyerson,2000:i-xx)። በቤተመንግሥትና በተዋረድ የጋብቻ ትስስርም ወደ አንድኛው እምነት በመግባት በሁለቱ አማኞች መካከል ይደረግ እንደነበር መታዘብ ይቻላል። ይህ ቢያንስ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ በስፋት የተስተዋለ ለሰላም ለትስስርና ለዝምድና ጭምር የሚደረግ እንደነበረ መረዳት አያዳግትም። በተጨማሪም አንዱ የሀገር ግንባታ ሂደት አካልም መሆኑን የሚያሳየን ነው (ጎይሌ፣ 2017፤ Beckingham and Huntingford, 1958: 190-251)።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ስለአብሮ መኖርና ጉርብትና ጉዳይ ጀሮሜ ሎቦ የተሰኙ ሌላው የፖርቹጋል ሚሲዎናዊ በጆንሰን በተተረጎመ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚሉት፣

| | |
|---|---|
| "Despite Christianity is the reigning religion…. Abyssinian provinces are inhabited by moors [Muslim], Pagans, Jews with similar historical standing"(Johnson, 2007: 30 በተጨማሪ Tellez, 1710፡39) | [ምንም እንኳን ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት ቢሆንም በኢትዮጵያ ግዛቶች እስላሞች፣ ሀገር በቀል እምነትና የአይሁድ እምነት ተከታዮች ሁሉም አብረው ይኖሩ ነበር...] |

በማለት ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እንዲሁም ፖሊቲካዊ መስተጋብር በልዩነት ውስጥ ተግባብቶ አብሮ የመኖርን ጥግ እንድንታዘብ ያስመለክቱናል። ይህንና መሰል የታሪክ ዘርፍ የውጭ ተጓዦች መዝግበው ያቆዩት ያዩተን፣ የኢትዮጵያ ሊቃውንትንም ጠይቀው አስተርጉመው እንደሚጽፉት መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም። ስለሆነም ይህ መረጃ ስለዘመኑ የሚሠጠን ግንዛቤ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለምሳሌ፤ በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ጎንደር የመጣውና የተወሰነ ጊዜ የኖረው አልሃይሚ የተሰኘው የመናዊ አምባሳደር በስፋት የክርስቲያኖችንና ሙስላሞችን አብሮ የመኖር ጉዳይና ሌሎች ተዛማጅነት የነበራቸውን ነገሮች በስፋት ከታች እንደሚነበበው አመልክቷል (Donzel, 1986)።

አልሃይሚ የኢትዮጵያዊያንን ሰው ማክበር፣ ትኅትናና መሰል ባህል በንጉሡ ምክንያትነት ባግራሞት እንደሚከተለው ይናገራል፡

| | |
|---|---|
| "... the king came dowm from his throne and sat on the floor a thing which I would not do unless the envoye is of the highest rank and entitled to the most glorious kind of honor......" (Donzel, 1986:61) | [ንጉሡ እንግዳ ከማክበሩ የተነሣ ከዙፋኑ ተነስቶ ወደ እንግዳ መቀበያው በመውረድ አነጋገረን። ይህን እኔ ብሆን የማረገው አይመስለኝም። በንጉሡ ደረጃ ያለን ሰዎች ስላልሆን ይህ ክብር የሚገባን አይመስለኝም . . . ] ። |

እዚህ ላይ የንጉሡን ትኅትና የተሞላበት አቀባበል በተመለከተ አልሃይሚ ያልተረዳው ነገር ያለ ይመስለኛል። እርሱ እንደመሰከረው የኢትዮጵያ ባህል አንዱ ዘርፍ ሊሆን እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደለም። ሆኖም ግን የአልሃይሚ ጉዳይ "የእግዚአብሔር እንግዳ ቤት ለእንግዳ "የሚለውን ጥልቅ የሀገር ባህል ከመተግበርም በላይ መልዕክት ያለው ይመስላል። ይኸውም የየመንን ንጉሥና ሕዝብ ወክሎ የመጣ አምባሳደር ስለሆነ ነው። የየመን ንጉሥ ጎንደር በሚገኘው የኢትዮጵያ ቤተመንግሥት እንደመጡ ተቆጥሮ አቻ ክብር እንደሚገባው አፄ ፋሲል እንደተረዱትና ለአልሃይሚም ያንን ማድረጋቸውን እንደ አምባሳደር የተገለጠለት አይመስልም። ያም ሆነ ይህ የነበረውን የቤተመንግሥት ሥርዓት በዐይነኅሊናችን እንድናይ የአልሃይሚ ዘገባ ይረዳናል። ሌላው የአልሃይሚ በጎንደር ሲባጅ ያስገረመውን ነገር አለፍ አለፍ እያለ ያስታውሳል፤

| | |
|---|---|
| ..... Some of the Christian eclassiatic spokeArabic, Khatirus was one and the leading. He spoke Arabic and showed interest in Islamic conversation ... Khatirus kept coming back even said that were it not that he did not feel free to do because of his position, he would accompany the ambassador to the Yemen, provided he could keep his religion. Alhaymi then pointed out that many Jews, and christians came to the Yemen for protection and safety, some remaining while paying ajeza others returning to their country after a short stay...." (Donzel, p.65) | [ . . .አንዳንድ የክርስትና እምነት ሊቃውንትን አጋጥሞኝ በተለያየ ነገር ላይ አውግተናል። 'የጴጥሮስ' ነገር ግን ልዩ ነበር። ተግባቢ ነው። እየተመላለሰ ይጠይቀን ነበር። ኃላፊነት ባይኖረው ኑሮ ሃማኖቱን በማይነካ መልኩ አብሮን የመን ሂዶ ለመጎብኘት ፈቃደኛ መሆኑንም ገልጾልን ነበር። እኔም ስለየመን አይሁዶችና ክርስቲያኖች ለደህንነታቸው ለኑሮ የመንን እንደሚመርጡ አንዳንዶቹ ሲፈልጉ ለሀገሩ ምስጋና እያቀረቡ ሲኖሩ ይስተዋላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ይመለሳሉ በማለት ገለጽኩለት . . . . ] |

እውቀትን ዝምድናን ፍለጋ ሰውን በሰውነቱ ማክበር የሚሉትን ጉዳዮች አልሃይሚ ከጎንደር አካባቢ የነበረውን ሁኔታ ከመንገሩም በተጨማሪ ሀገሩ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ የተለያየ እምነት ያላቸው ሰዎች ተከባባረው እንደሚኖሩ ፍንጭ ሰጥቷል። ምናልባትም ይህ ነገር የሚያሳየን የሰው ልጅ ፍላጎት እሳቤ እንደመልኩ አመሉ ልዩነት ስላለው ተስማምቶና ተግባብቶ መኖር ተፈጥሯዊ ግዴታም መሆኑን ነው። ይህ አስተሳሰብ ዓለማቀፋዊ እውነታነትም ያለው ሲሆን፣ ነገር ግን በተግባር እምብዛም አይስተዋልም። ይህም የሰው ልጅ አመል ከስንት አንድ እንጂ ራስ ወዳድነት የሚያጠቃው በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም። ግን ይኸን ሁሉ ነገር የሚገራው ምግባር መንፈሳዊ ወይም ሞራል የሚባለው በሰዎች ውስጥ ሲሰርጽ ብቻ ነው። ይህ ተግባር በቀድሞ ኢትዮጵያዊያን የቀን ተቀን ውሎ ላይ የስተዋል ነበር ለማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ በአዲያም ሰገድ እያሱ ዘመን መጥቶ የነበረው ፖንሴት የተሰኘ ፈረንሳዊ የሕክምና ሊቅ በበኩሉ በጎበኛቸው ቦታዎች ሁሉ ለምሳሌ፤ እንፍራንዝ፣ ጎንደር ከተማም በሌሎችም በተዘዋወረባቸው አካባቢዎች በሙሉ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ተባብረው ተሳስበው እንደሚኖሩ ጽፏል (Poncet, 1949)። እስኮትላንዳዊው የአስራ ስምንተኛው ክፍለዘመን አሳሽ ጀምስ ብሩስ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በተለያየ ዘርፍ የሥራ መስተጋብር እንደነበራቸው ተናግሯል። ምግብም ከሥጋ በስተቀር አብረው እንደሚመገቡና የሚለያቸው እንደሌለ ይናገራል (Bruce, 1790: 197-198, 362- 185)።

በአሥራ ዘጠነኛውም ሆነ በሃያኛው ክፍለዘመንም በተለያየ የኑሮ ዘርፍ ይኸው መስተጋብር ከሃይማኖት አባቶች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ሹማምንት እስከ ተራው ሕዝብ ልዩነቶቻቸውን አክብረው አብረው በጉርብትና በጋራ በመሥራት በመጠቃቀም እንደኖሩ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ ( Rassam, 1869; Abdussamed, 1989 ; Bahru,2023; John 2016)፡ ፡ ይህ ሁኔታ በተዋረደ "ሀገር የጋራ ሃይማኖት የግል" በዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ጊዜ ጀምሮ እንደ አዋጅ የተነገረ ከዚያም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴም በዚሁ አግባብ ጸንቶ እንደተኖረ ይነገራል (መረጃ ሰጪ፣ ሼህ መሐመድ ራጃ፣ አሰበ ነጋሽ፣ ባዩህ በዛብህ)። ባንድ ወቅት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስለ ዘመናዊ ትምህርት ለዜጎች አስፈላጊነትና ዜጎችም በአብሮነትና በመተባበር መኖር እንዳለባቸው መንግሥታቸውም በዚያ መልክ እንደሚሠራ የተናገሩትን ማስታወስ መልካም ነገር ይመስለናል፤

> ኢትዮጵያ ወገን ያልተለያየባት አንድ ቤተሰብ ሆና ሕዝቡ በአንድ ሕግ ተወስኖ ባንድ ንጉሠ ነገሥት ተገዝቶ በመተባበር ኀይል የበለጠ እንዲሆን . .ሁሉንም የሚያደላድል እውቀት ስለሆነ . . . .የስላሞቹም የክርስቲያኖቹም ልጆች የአባቶቻቸቸውን ሃይማኖት እንደያዙ ሀገራቸውን የሚጠቅሙበትንና መንግሥታቸውን የሚያገለግሉበትን ራሳቸውንም የሚረዱበትን እውቀት እንዲማሩ አደረግን እንጂ እንዲለያዩ አላደረግንም።. . .ለሰው ልጅ ሃይማኖቱ የግል ጉዳዩ ሲሆን፣ ደግሞ ጠቅላላውም ጉዳይ የሚጠበቅበት . . . . . የሀገሩ ነፃነት ነች።. . .ነፃነት ስትጠፋ በክርስቲያኑም በእስላሙም ላይ የባርነት ቀንበር ማስከተሏ የታወቀ ነው. . . (አክሊሉ፣2017፡ 263)።

ከላይ የተጠቀሱት የመረጃ ጥንቅሮች የሚያሳዩን በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የነበረውን  አብሮነት፣ መቀራረብ፣ መደጋገፍ፣ መተሳሰብና መዛመድን ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በጋራ በልዩነት ውስጥ ተከባብሮ ለመኖር የሚያስችል በነበረው የማኅበረሰብ እሴት ላይ በሂደት ዘመናዊ ኢትዮጵያን አፄ ምኒልክ ተጸናች በኋላ የበለጠ የሚያስተሳስረው የሚመስለውን የዜግነት ሙብት እየተጨመረ እንደመጣ መገንዘብ ይቻላል።

## ፪. የሃይማኖት አብሮነትና መተሳሰብ በጎንደር ክፍለሀገርና አካባቢው

ጎንደር፣ ሦስቱ የአብርሃም እምነቶች የሚባሉት አይሁድ፣ ክርስትናና እስልምና በጋራ የኖሩበት አካባቢም እንደሆነ ይገለፃል (Debash, 2011; Gerard & Éloi (edit.)2015:5)። አካባቢው ከሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብት፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የመሳሰሉት ማእከል ነበር። እንደ ሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ሁሉ በሃይማኖት አብሮነትና መከባበር ተጠቃሽ ነው (John, 2016;  ቃለመጠይቅ፤ ባዩህ በዛብህ፣ ምስጋናው አይቸው፣ አሰበ ነጋሽ)። ይህን አብሮነት በከፊል ለማስተዋል  አዲያም ሰገድ እያሱ (1682-1706) ሲሞቱ በሕዝቡ ላይ የነበረውን ሐዘን መንፈስ ዜና መዋዕል ጸሐፊው እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፤

| በግእዝ | አማርኛ ትርጉሙ |
|---|---|
| በከመ፡ በከየ፡ በሞተ፡ አቤሴሎም፡ ንጉስ፡ እስራኤል፡ ዳዊት። ወዳግመ፡ በከዩ፡ ወዓልተ፡  ንጉሱ፡ ተያይዘው፡ አንገት፡ ላንገት፤ ቢሞትባቸው፡ ድንገት፤ አሉ፡ አሉ፡ ሲሉት፡የለመዱ፡ ሹመት፤ ያልተሾሙ፡ በከብት፤ ከፍ፡ ያሉትም፡ በጉልት። ወዘንተ፡ ብካየ፡ ዘርአየ፡ ወሰምዓ፡ እምነ፡ ጎንደር፡ እስከ፡ ወሰነ፡ ምድር፤ እስላም፡ ወአምሃራ፤ ቅማንት፡ ወፈላሻ፤ ወታደር፡ በጋሻ፤ መነኩሴ፡ በዋሻ፤ ነጋዴ፡ ሰው፡ ሳይሻ፤ የሚሄድ፡ በጣሻ በከየ፡ ወአስቀቀወ። በስመ፡ በከዩ፡ አርድእት፡ በሞተ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ዘሎቱ፡ ስብሀት፡ ሳህሉ፡ ወምህረቱ፡ የሃሎ፡ ምስለ፡ ፍቁር፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን | …የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት በልጁ በአቤሴሎም ሞት እንዳለቀሰ ዳግመኛ የንጉሥ ኢያሱ አገልጋዮች አለቀሱ። ተያይዘው አንገት ላንገት ቢሞትባቸው ድንገት አለ አለ ሲሉት። የለመዱ፣ ሹመት ያልተሾሙ፣ በከብት ከፍ ያሉትም፣ በጉልት፡ ፡ ይህን ሐዘን (ለቅሶ) የተመለከተና የሰማ ከጎንደር እስከ ምድር ዳርቻ (ወሰን) ድረስ እስላምና አምሐራ (ክርስቲያን) ቅማንትና ፈላሻ፤ ጋሻ የታጠቀ  ወታደር፣  በዋሻ የሚኖር መነኩሴ፣ ሰው ሳይሻ  በጫካ የሚሄድ ነጋዴ (ነጋዴ፡ ሰው፡ ሳይሻ፤ የሚሄድ፡ በጥሻ) ፤ አነባ፤ አለቀሰ። በጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ሞት ደቀመዛሙርቱ እንዳለቀሱ (እንዳዘኑ) ፤ የእርሱ ምስጋና፣ ምህረትና ርኅራሄ ከወዳጁ ጋር እስከ ዘለዓለም ይኑር ! አሜን ! (ደሳለኝ፣ 2014 ዓ.ም.)። |

| | |
|---|---|
| "…Mohamedans joined the king at the time of war ....." Bruce further gave abit exaggerated witness that "...there was not a man in Abbyssinia that was abraver soldier and better horse man than Yassine,that he had no love for money but was a man of probity and honour…… " (Bruce, 1790:361-2). | ትርጉም፤ "..ሙስሊሞች ንጉሡን በጦር ይራዱ ነበር.." እዚህ ላይ ብሩስ የተጋነነ የሚመስል መረጃ በያሲን ምሳሌነት የሰጠ ቢመስልም የታዘበውን እንደሚከተለው ይለናል፡፡ ".[.በኢትዮጵያ ምድር እንደ ያሲን ዓይነት ጀግና ወታደር፣ ፈረስ ጋላቢ፣ ሐቀኛ፣ ገንዘብ የማይወድ የተከበረ የለም...."] |

ሌላው የዘመኑ ሰነድ አ.ኤ.አ. 1769-1840 የነበሩ ነገሥታት ዜና መዋዕል ንጉሡ ከአይራ ሲነሱ ካህናቱ በዝማሬ ሲቀበሏቸው መላ ሕዝበ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ በእልልታና በዘፈን በጭፈራ ተቀበሏቸው ይላል (Blundell, 2007: 214) ። ይህም የአብሮነትንና ውኅደትን መንገድ የሚያሳን ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አይሆንም።

ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ የክርስትናና የእስልምና እምነት አባቶች የሥነምግባር የሃይማኖት ጠባቂዎች የሀገር ፍቅርም አስተማሪዎች ስለነበሩ በሀገርም ሆነ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ሚናቸው የጎላ ነበር። ከባድም ይሁን ቀላል ችግሮች ሲፈጠሩ በጋራ ተመካክሮ የመፍታት ባህል እስከ ቤተመንግሥት ድረስ የሁለቱም የእምነት አባቶች ሚና ትኩረትን የሚሻ ሆኖ ይገኛል። "ቄሱ በጭራው፣ ሼሁ በቁርቁራው ይዳኝ ነበር" እንዲሉ። ለምሳሌ፤ በቤተመንግሥት በባለቤታቸውና በእንጀራ ልጃቸው ራስ ዐሊ ሥልጣን ተሸፈንኩ በማለት የተከፉ የሚመስሉት አጼ ዮሐንስ ሳልሳዊ ሸፍተው ወደ ጫካ ሲያመሩ ተይዘው ለራስ ዐሊ ይሰጣሉ። ራስ ዐሊም ንጉሡን ከወታደር ጋር አቆራኝተው ወደ ጎንደር ባለቤታቸው ጋር እንዲታሰሩ ለእቴጌ መነን ይልካሉ። በሁኔታው የጎንደር ሕዝብ ይጨነቃል። እቴጌይቱ ባላቸውን ቢወዱም በሁኔታው ግን በመሸፈታቸው እንደተበሳጩ በወቅቱ የነበረው አርኖልድ ይገልጻል (ገነት፣ 2013)፡፡ ገነት የተረጎመችው ይኸው የአርኖ ሚሸል ዲአባዲ መጽሐፍ ትዝብቱን እንደሚከተለው ያስነብባል፤

> ..ወሬው እንደተሰማ ከተማዋ ከዳር እስከዳር ተነቃነቀች። አቡኑ በታላላቅ ሰዎች ታጅበው ሲመጡ አልባሰ ተክህኖ የለበሱ ወደ አሥራ ሁለት የጎንደር አድባራት ካህናትና ቀሳውስት አስቀድመው እጨጌው ተከተሉ። በመቀጠል የዑለሞቹ መሪ ሼህ ዐሊ፣ ቃዲውን ሙፍቲውንና ኢማሙን እያጀቡ ሲሄዱ ሕዝበ ሙስሊሙ በቅርብ ርቀት እያጀባቸው ተመመ። ሙስሊሙ ሰልፈኛ ሰንደቅ ዓለማውን ከፊቱ አስቀድሟል፡፡ አቡኑ፣ እጨጌውና ሼህ ዐሊ ከእቴጌይቱ ቤት አካባቢ ካለው አደባባይ ከበቅሎ ሳይወርዱ ቆም አሉና መልዕክት ላኩ፣.....እቴጌም...ለምን ደከማችሁ? እኔ ወደናንተ እመጣ ነበር እኮ?.... በመጨረሻም ለሽማግሎዎቹና ለሕዝቡ ባላቸው ፍቅር ለባላቸው ይቅርታ አደረጉላቸው.... (ገነት፣ 2013፡ 62)።

ባልና ሚስቱም በሂደት የቀድሞ የፍቅር ሕይወታቸውን እንደጀመሩ ተገልጧል።

ምንም እንኳን ዘመነ መሳፍንት ተብሎ የሚጠራው የኢትዮጵያ የታሪክ አካል የእርስ በእርስ ግጭቶች መከፋፈል የበዛበትና ማዕከላዊ መንግሥት የተዳከመበት ሕዝብ ችግር ውስጥ የነበረበት ቢሆንም በዘመኑ ትልቅ ሥልጣን የነበራቸው የየጁ መሳፍንት ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ ወገን ማገናኘቱን አጠናክረው የቀጠሉበት ይመስላል፤

| | |
|---|---|
| .....Whenever historians discuss the ruling class especially those of the Zämänä Mäsafent, they tend to focus on their divisive characteristics. .... They were all interrelated either by blood or marriage.... Ali I himself was the son of Séru Gwangul of the Wârâ Séh while through his mother he was related to Ras Faris of Lasta. When he died in June 1788 he was buried in Lalibela because Lasta was as much his “country” as Yâju. His sister Kâfay was married to Mârso Bârénto, chief of a Wâllo Oromo... Gugsa’s daughters were married to Maru of Dambeya, to Dajač Wâldâ Rufaél of Meça (Gojam), to Wagšum Kenfu and to Däjač Haylâ Maryam of Semen. The latter had three children from Hirut Gugsa-Mârso, Betul and Yâwbdar. Yâwbdar was married to Subagadis and her two young brothers stayed with her in Tegray after their father died. Later, they came to their cousin’s (Ali II) court at Dâbrâ Tabor where they lived most of their lives. Ali II himself was the son of Mânân, member of the Mamâdoc family of Wârâ Himâno and Wâlo... All the provincial ruling ‘houses shared two characteristics: inter-relationship and continuity which incidentally has always been the trait of power elites throughout history. The Mamâdoô family was inter-related by blood & marriage with practically every province in the Mâsfenate. The case of the Wârâ Séh rulers is already wellknown. There was no ruling house not related to them Taytu would be a typical case in point in that family. She was as much a member of the Wârâ Séh as of the Semen house; her mother was from Gojam and her aunt was married to Subagadis. Yâju, Lasta, Wâlo, Bâgémder, Meça (Gojam), Semén were all her “countries”. In her later life, there was practically no family of importance to which she was not related either by blood or marriage....... (Shiferaw,1990: 162-1633) | ትርጉም፤ ብዙ ጊዜ የታሪክ ተመራማሪዎች ዘመነ መሳፍንት የተሰኘውን የሀገራችንን የታሪክ ምዕራፍ ብያኔቸው የመከፋፋል ዘመን አድርገው ይገልጹታል. . . .። ነገርግን በወቅቱ ከፍተኛውን የሀገሪቱን ሥልጣን ይዘው የነበሩ የየጁ/ ወረሸህ/ መሳፍንት ያልተዋለዱት፣ ያልተጋቡት ባላባት አልነበረም። ለምሳሌ፤ ቀዳማዊ ራስ ዐሊ የሴሩ ጓንጉል ልጅ በእናቱ ከላስታው ባላባት ራስ ፋሪስ ጋር ይዛመዳል። እ.ኤ.አ.1788 ሲሞት የተቀበረው ቅዱስ ላሊበላ ነበር። ስለሆነም ልክ እንደየጁ ሁሉ ላስታም የራሱ ሀገር ሊባል ይቻለዋል። እህቱ ወ/ሮ ከፋይ የወሎውን ኦሮሞ ባላባት መርሶ ባሬንቶን አግብታ ነበር። የራስ ጉግሣ ሴት ልጆች አንዷቷ ደጃች ማሩ የተባሉትን የደንቢያ ባላባት፣ ሌላዋ ደጃች ሩፋኤል የተሰኙትን የሜጫ ጎጃም ባላበት ስታገባ ሌሎች ሁለት ደግሞ አንዷ ዋግ ሹም ክንፋን፣ ሒሩት የተሰኘችው ደግሞ የስሜኑን ደጃች ኃይለማርያምን አግብታ ነበር። ከስሜን የሚወለዱት ሒሩት፣ ጉግሣ፣ መርሶ፣ ቡጡልና የውብዳር የተሰኙ ሲሆን፣ የውብዳር የትግሬውን ባላባት ሳባጋዲስን አግብተው ሲኖሩ ሁለቱ ወንድሞቿ አብረዋት ይኖሩ ነበር። ኋላ ወደ ደብረታቦር ከአጎታቸው ልጅ ከትንሹ ራስ ዐሊ (ዳግማዊ) ጋር አብረው ኑረዋል። ራስ አሊ ዳግማዊ እንዲሁ በናታቸው የወሎ መሃመዶች ሲሆኑ፣ ባባታቸው አሉላ ደግሞ የጁ ወረሸህ ናቸው። ከነዚህ ቤተሰቦች ያልተጋባ ያልተዋለደ አልነበርም። እቴጌ ጣይቱ ጥሩ ምሳሌ ናቸው። ለኋለው ትስስርና ዝምድና ወረሸህ፣ ጎጃም፣ ስሜን፣ ወሎ፣ በጌምድር፣ ትግሬ ሁሉም ሀገራቸው ነበር። በደም ያልተሳሰራቸው አልነበረም. . . .። |

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኀይሌ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደምና በሥጋ ብቻ ሳይሆን በእምነትና በባህል መወራረሱንና መዋሐዱን ዘመን መሳፍንት የተሰኘውን የታሪክ ክፍል እንደምሳሌ ጠቅሰው ያስረዳሉ፤

> .....የጁዎች በክርስቲያን ቤተመንግሥት ተቀምጠው እስላሞችን ሲያገቡ ሴቶቹን ያክረስትኗቸው እንደነበረ፣ በዚያው ልክ የወሎዎቹ ሙሃመዶች ደግሞ እስላሞች እንደመሆናቸው ከክርስቲያን ሚስቶቻቸው ያጋቡ የነበሩት እያሰለሟቸው ነበር። ሁለቱም በዝርያቸው ከኦሮሞ ብሔረሰብ እንደመሆናቸው ሁናቴው የሚያሳየው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደምና በሥጋ ብቻ ሳይሆን በእምነትና በባህል መወራረሱንና መዋሐዱን ነው (ኀይሌ፣2017፡ 9)

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች የምንታዘበው በየትኛውም አግባብ ከልዩነት ይልቅ መደጋገፍን፣ ዝምድናን መሰናሰል የበዛበት ታሪክ መኖሩን ነው። ይህ የመዛመድ ባህልም ከጥንት የመጣ መሆኑን ወደ ኋላ መለስ ብሎ ታሪክ ማስተዋል ተገቢነት እንዳለው የሚያጠራጥር አይሆንም።

በመሃዲስት ወረራ ጊዜ (1888) በርካታ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳት በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ተሰብስበው ኋላ ለክርስትና አማኝ አባቶች እንደተሰጡ የአካባቢው ታሪክ ዐዋቂዎች ያስረዳሉ (ቃል መረጃ ሰጪ፤ ሏሊህ መሐመድ፣ 2011ዓ.ም.፤ ከድር ታጁ፤2012 ዓ.ም.፣ ሼህ ሰይድ አበደልቃድር፣ በያን ገበያው)። የሼህ አብዱልባሲጥ በአጼ ፋሲል ጊዜ የታወቁ ወልይ መቃብራቸው አዘዞ ሎዛ ማሪያም ቤተክርስቲያን አጠገብ የሚያሳየን ከክርስቲያን ወገኖቻቸው ጋር የቀረበ ወዳጅነትና ፍቅር እንደነበራቸው ነው። ከአዘዞ ተክለሃይማኖት ገዳም አባቶችም ጋር ፍቅራቸው ልዩና ምስጢረኛም ነበሩ (አስቻለው ከፋለ፣ አህመድ የሻው፣ ማለደ ሞገስ)። የእኚሁ አባት መውሊዳቸው ፋሲካ በዋለ ሰልስት ማክሰኞ ይከበራል። የሼህ ዐሊ ጎንደር መውሊድ፣ ደባርቅ ሼህ ሃዘል እንዲሁ በተመሳሳይ ጊዜ ይከበራል። በለሳ ደንግ ጎንድ ተክለሃይማኖት አንድ የበቁ አባት "ሼህ ጎብር እስማኤል" የተሰኙ ከገዳሙ አጠገብ መቃብራቸው ተጠብቆ ጫካ ሆኖ በሙስሊም ክርስቲያኑ ተከብሮ የሚኖር ሲሆን፣ በተንሳኤ ሳምንት መውሊዳቸው ይወጣል። የመቃብራቸው አፈር እምነት ነው ተብሎ ስለሚታመንበት በክርስቲያኑም በእስላሙም እንደ መድኃኒት የቀጠራል። የሼህ አባድር ጎንደር መታሰቢያ ቦታ ላይ የፋሲካ እለት መውሊድ ይወጣበት ነበር (ዝኒከማሁ)። ደምቢያ ቸንክር ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያንና የሼህ ጅብሪል ታሪክም ሊጠቀስ የሚገባው ነው። የመሃዲስት ወታደሮች ደብሩ ላይ አደጋ ለማድረስ ሲገሰግሱ የሀገራቸው የመከባበርና የመጠባበቅ መንፈስና የፈጣሪ ኀይል አግዟቸው ሼህ ጅብሪል ከደብሩ ደጃፉ በመስገድ የርሳቸው ቤተእምነት እንደሆነ አስመስለው በመናገር ለጥቃት የመጡትን ወታደሮች አልፈው እንዲሔዱ እንዳደረጉና ቤተክርስቲያኑን ከጥፋት እንዳዳኑት በአካባቢው በስፋት ይነገራል (መረጃ ሰጪ፤ ቄስ ምስጋናው፣ ሼህ ሰይድ ፣ 2015 ዓ.ም. ቸንክር ደንቢያ)፡ ፡ አሁን ቦታው ምንም እንኳን ክርስቲያኖች የሚኖሩበት አካባቢ ቢሆንም መታሰቢያቸው ይሆን ዘንድ ግን ቦታው "ጅብሪል ጎጥ"፣ አንዳንዴም "ጅብሪል ተራራ" እየተባለ ይጠራል። ምናልባትም ሼሁና ቤተሰቦቻቸው በተክለሃይማኖት ገዳም ጎረቤት ይኖሩበት የነበረው ቦታ እስከሁን ተከብሮ ይገኛል። ከአካባቢው በርካታ ሙስሊሞች በንግድ ሥራ ከተማን መርጠው ከተማ ገብተው ይገኛሉ (ባዩህ በዛብህ፣ ቄስ ምስጋናው፣ ሼህ መሐመድ አደም 2/3/2013 ዓ.ም.)።

ስማዳ ወረዳ ልዩ ስሙ አራጣ በሚባለው አካባቢ ጌታው ሼህ ቀሪብ አህመድ የተባሉ ወልይ ከፈጣሪያቸው፣ ከመንግሥታቸው፣ ከማኀበረሰቡና ከቅርብ ጎረቤታቸው አራጣ ገብርኤል ደብረ ገነት ቤተክርስቲያን ካህናት ጋር የነበራቸውን ወንድማዊ ግንኙነት የፍቅር ተዓምራት የሚያስደምም ነበር፤ አምላክ ከፍቅር ጋር ነው እንዲሉ። ከነበራቸው ፍቅርና ቤተሰባዊነት የተነሣ ቤተክርስቲያኑም መስጅዱም ጎረቤት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ያረፉበትም ቦታ እኩል መሆኑ ነው። ይሄም ብቻ አይደለም ጌታው[3] ቀሪብ አህመድ በደቀመዝሙሮቻቸው (ደረሶቻቸው) ታጅበው ከነሙሉ ክብራቸው ከካህናቱ ጋር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በሥዕል ተስለው ይገኛሉ። ይህ ሥዕል ምናልባትም በጎንደር ዘመን በተለይ በአፄ ኢዮያም ሰገድ እያሱ ጊዜ ተስፋፍቶ የነበረው የኪነጥበብ ሥራ አካል ሳይሆን አይቀርም። የአካባቢው ታሪክ ዐዋቂዎች ግን ወቅቱን ወደ 1268 ዓ.ም. ይወስዱታል። ሼኩ ለሀገሬው ሕዝብ ለመንግሥት በበርካታ መንፈሳዊና ዓለማዊ ግልጋሎታቸው የሚታወቁ ነበሩ። አካባቢውንም በርሳቸው ግልጋሎት የተነሣ የአራጣ ሀገር ሰው ግብር እንዳይከፍል ተደርጎም ነበር። ይህን ተከትሎ "በአራጣ የለም ግብር፣ በሰማይ የለም ዱር" እየተባለ እስከሁን ድረስ ይነገራል። የአካባቢው ሰው አሁንም ይህንኑ የትብብርና የፍቅር ታሪክ ጠብቆ እንደሚኖር መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ (ቃለመጠይቅ፤ አለሙ አልዩ፣ ሼህ መሐመድ አበበ፣ መኳንንት ገበየሁ)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ 1954 ዓ.ም. ለበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዥ ደጃዝማች አምሃ አበራ የተጻፈ ማመልከቻ፤

---

3 "ጌታው" ጨዋ፣ አለቃ፣ ዐዋቂ፣ ክቡር፣ በዐረበኛ ሰይድ የተሰኘ ተርጓሜ ሊኖረው ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ "ጌታው" ሲባል ፈጣሪን /አምላክን ለማሳነስ ወይም እሊህ የበቁ ሰው የፈጣሪ በረከት አድሮባቸው ልመናቸው ተሰምቶ አላህ/ እግዚአብሔር ጉዳያቸውን ቢከውንላቸው እንደክብር ያገሬው ሰው ጌታው ቢላቸው ከፈጣሪ ጋር ተወዳደሩ ተሻረኩ ሊባል አይገባም፡ ፡ የኛ ሰው ሙስለሙም ሆነ ክርስቲያኑ እንደ ባህል እንኳን እርሳቸውን ይቅርና ሌላውንም ሰው " አጌታው" የማለት ልማድ ያለው ሕዝብ ነው (ቃለመጠይቅ ሼህ አህመድ ሸረፋ፤ አስቻለው አለነ)፡፡

"...ስሜ ሼህ አብደል ባቂ ያባቴ ስም ግራዝማች መሐመድ ያሲን....አገሬ ደብረታቦር፣ እስቴ አሬጣ ገብርኤል ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ሃይማኖቴ እስላም ሥራዬ ያባቶቼን የነጌታው ሼህ ኢማን መስጂድ ጠባቂና ለሀገሬና ለንጉሠ ነገሥቴ ጸሎት አድራጊ....። ክቡር ሆይ ከርብ እስከ መሸሎ የቃዲነት ሹመትና የሃይማኖት ሥነሥርዓት አጠባባቅ ከአፄ አለም ሰገድ እያሱ ዘመን መንግሥት ጀምሮ እስከ አባቶቻችን እኛም እስከደረስንበት 'በጥንቱ መሠረት' አስፈቅደን የያዝነው ለመሆኑ ማስረጃው ከዶሴያችን ጋር ከዚሁ ይገኛል:: ....ስለዚህ ክቡር የፍርድ ሚኒስቴር ሥራውን እንዲፈቅድልን በማለት እስከ ዛሬ በየጊዜው ለዚህ ጠቅላይ ግዛት..... እንዲሁም ለክቡር ያገር ግዛት ሚኒስቴር ለክቡር ለከፍተኛው የሸሪኣ ፍርድ ቤት ለብዙ ጊዜ አሳስበናል...።

ከዚህ ላይ የምንረዳው መተዋወቅን አብሮ መኖርን ዕውቅና የመስጠት ጉዳይን መተሳሰብን መከባበርን መረዳዳትንና የመሳሰሉትን የሰው ልጅ ባሕሪያትን ከላይ እስከታች ከመንግሥት እስከ ማኅበረሰቡ የሚያመለክተን ነው። በተጨማሪም ምንም እንኳን ነገሥታቱና በተዋረድ አስተዳዳሪዎች ክርስቲያኖች ቢሆኑም ለእስልምና እምነት ተከታይ ሕዝባቸው የሃይማኖት አጠባበቅ ሥነሥርዓት ጉዳይም እንደሚያሳስባቸው የሚያስረዳንም ነው። ሌላው ግራዝማች መሐመድ የተሰኙት ግለሰብ ለመንግሥትና ለሀገር ለየት ያለ ግልጋሎት እንደነበራቸው የሚያመለክተን ነገር ያለ ይመስላል። "ለሀገሬና ለንጉሠ ነገሥቴ ጸሎት አድራጊ" ከተባለው መልካም ቃል አለፍ ያለ ከመንፈሳዊነት ባሻገር በአካል መስዋዕትነት የሚያስከፍል አንድ ዜጋ ለሀገሩ ሊሠጥ የሚገባውን ምናልባትም የወታደራዊ ግልጋሎት እንደነበራቸው የሚያስገነዝብ ነው። በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ ሁሉም ሰው በሚባል ደርጃ ወታደር ነበር። በየዘርፉ በተሰጠው ሥራ ይሳተፍ ነበር። "ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት" ሲባል ማቄን ጨርቄን አይባልም የሀገር ነገር ነውና። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአደዋ 1888 ዓ.ም. ዘማችም ነበሩ የሚሉ መረጃች አጥኝው አግኝቷል (ቃለመጠይቅ፤መኳንንት ገበየሁ፣ ኸድር ታጁ፣ አባ ሸኩር አህመድ፣ አሰበ ነጋሽ፣ አለሙ አልዩ፣ ሼህ መሐመድ አበበ)። በተለያዩ አስቸጋሪ ፈተናዎች ውስጥ የዚህ ዓይነቱን መቀናጀትና መተባበር በየፈርጁ መሳተፍ ረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየን ብርቱ ጉዳይ ነው።

እንደተባለው ይህ መሰናሰል በታሪክ መነጠር ይስተዋላል፤ ቀጣይነትም ነበረው። ለምሳሌ፤ ሀገራዊ ኃላፊነቶችን መጋራት፣ የሀገር ፍቅር ማኅበር (የጀግኖች ማኅበር)፣ ተወላጅነት፣ የርስት ተካፋይነትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። እዚህ ላይ የአንድን አባት ማመልከቻ እንጥቀስ "እኔ ነጋድራስ ዐሊ ሐሰንና ሼህ ለጋስ አደም በምንከራከርበት እንደቢናና በደርኪ ጭቅነት ካሁን በፊት በቁስቋም ደብረ ጸሐይ ባለቃውና በማኅበሩ ማኅተም መወለዴን በማረጋገጥ ለጉባዔ መንፈሳዊ ጽ/ቤት ጽፈውልኝ በዚህ መሠረት ማዘዣ ተሰጥቶ ማሩን ከፍዬ ፊታውራሪ ጣሹ እንግዳ እጄን ሳያዞሩልኝ ወደ ስሜን ዘመቻ ሄዱ.....". በማለት የነበረውን ከሃይማኖት ልዩነትና መከባባር በስተጀርባ የስጋ ዝምድናን ኅብርነትንም የሚያሳየን ነው። ሌላው ቤተክህነት ከሃማኖታዊ ግልጋሎቷ በተጨማሪ ለማኅበረሰቡ ታሪክ እንዲጠበቅና ከትውልድ ትውልድ መተላለፍ የነበራትን የማይተካ ሚና የሚያስገነዝበን ሆኖ እናገኘዋለን።

የፈረንሳይ ሀገር ጥናት ተቋማት በ1920ዎቹ የታሪክና ባህል አጥኝና መረጃ ሰብሳቢ ልዑካን ቡድን "ከዳካር-ጂቡቲ" ዘመቻ አድርገው ነበር (Michel,1958)። ይህ የምርምር ቡድን በርካታ ጊዜውን ካሳለፈባቸው አካባቢዎች ጎንደርና አካባቢው ይገኝበታል። በዚህ ጊዜ ከተሰበሰቡት የታሪክ መረጃዎች አንዱ "ዘጥበብ፡ ታሪክ፡ ዘሰይድ፡ ዘተጽሐፈ፡ እም፡ ጎንደር" ይገኝበታል፡፡ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ከጎንደር ስመጥር ክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ እንደሆኑ ስማቸው ባይጠቀስም የአጻጻፉ ብስለትና ጥልቀት የቋንቋው ውበት ይነግረናል። አንዳንዴ ይህ ጽሑፍ በአንክሮ ለተመለከተው "ዜና መዋዕለ ዘሰይድ" ሊባልም ይችላል። ሰይድ የተሰኙት የፈጣሪ ጥበብ የተገለጠላቸው ግለሰብ ክርስቲያኑን፣ እስላሙን፣ ቤተእስራኤሉንና ሌላውንም የሀገር ሰው አምላክ በሰጣቸው ጥበብ ታግዘው እያከሙ ይፈውሱት እንደነበር በስፋት ተዘግቦ ይገኛል። እዚህ ላይ አባ ሰይድ ከዜና መዋዕል ጸሐፊያቸው ጋር የነበራቸው የእውቀት የጥበብ ቅርርብና ፍቅር አብሮ መሥራት የሚያስደምም ይመስላል። እንደኚህ ሊቅ አገላለጽ ሼህ አባ አማን ወሎ የጁ የነበሩ ትልቅ ሰው ሲሆኑ፣ ፈጣሪ ዐቅሙን (ቅዋውን) ሰጥቶ ለሕዝብ መድኃኒት ያስቀመጣቸው ነበሩ። ሁሉም እርሳቸውን ይታዘዛል፡፡ ሰይድን የመረቁና በጎንደር የሾሙ እርሳቸው ናቸው። እርሳቸውም በከዳማቸው/አጋፋሪያቸው/ ቡና ተፈልቶ፣ እጣን አጢሶ፣ ጮፌ ተንዘንዞ ወዳጃ[4] ም ተቀምጠው በጸሎት ሰይድን መረቁት በጎንደርም እንደሾሙት በስፋት ተገልጾ ይገኛል (Gallica Éthiopien, 592) ለዚህም ምስክርነት፤

..ዘጥበበ ሰለሞን ዘሰይድ ዘዐፅአ ጎንደር በዘመነ ዮሐንስ እስከ ዘመነ ማቴዎስ ሰይድ የሠራው ሥራው በሚካኤል ዛሬ ይወርዳል፤ እጣን ይጤሳል፤ ወዳጃም ይሰባል፤ ሁሉ የተመመው በሩቅ ሀገር በቅርብ ሀገር ያለው እርሱን እያለ ይሰበሰባል....። ፈጠነች የተባለች ሴት ታማ መጣች ሀገሯ አርማጩሆ ነው ። መጥታም ተሰይድ ገንዳ ወደቀች.... ተመሚም ዳነች። በተረፈ በቁመትሽ ለከተሽ ክታብ አሠሪ አላት። ፋጡማ የምትባልም ሴት ወደ ሰይድ ታማ መጣችበት....ከገንዳው ወደቀች መድኃኒቱን ሲያደርግላት ዳነች......ጥልፍ ቀሚስ፣

4 በሙያው የተካኑ ጓደኞቸች በባህሉ መሠረት ተቀምጠው የሚያደርጉት ያጋራ ጸሎት

አልቦ፣ ድሪ እንድትለብስ መከራት ፋጢማም ዳነች። ቤቷ እስላም ቤት[5] ነው። ለጌታው ያደረ ነውና ቅርቡ ነው፡ ፡ መድኃኒትሽ የፍየለፊጅ ሥር፣ የአጋም ሥር ሁሉን አድርጎ ዘፍዝፎ ጠመቃት ዳነች። ለወ/ሮ ጠጅቱም ቤቷ ቀኝ ቤት ጎንደር እርሷንም በአምላክ ፈቃድ አዳናት. . . ." (Gallica Éthiopien 592፡17-19)።

ከዚህ ዘገባም የምንረዳው በርካታ ቁምነገር አለ። ለምሳሌ፤ የሀገር በቀል እውቀትንና ሕክምና ዋነኛው ነው። በሙያው የበቁ አባቶችን ትብብርም ማየት ይቻላል። አባ ሰይድ ሙስሊም ቢሆኑም የሚያክሙት ሁሉንም ሰው ነው። ወደ እርሳቸው የሚሄደው ሰውም እውቀቱ ላይ እንጂ የእምነት ልዩነቱ ላይ ትኩረት አልነበረውም። በአጠቃላይ በሃይማኖት ተከባብሮ መኖርን ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊነት ላይ የተመሠረተ አሠራርን በመከተል በመንፈሳዊም ሆነ በምድራዊው ዓለም ያሉትን የሰው ልጅ አኗኗር በመመርመር በጋራ ለወገን ጥቅም እንዲውሉ ማድረጋቸውን እንረዳለን። ውጤታማም ለመሆን አብሮ ተግባብቶ፣ ተዘናንቶ መሥራትንም፣ እርስ በእርስ መተዋወቅንም፣ መማማርንም ሌላም ይህን የመሰለ የሥልጣኔ መንገድ ሥር ሰዶ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም የሀገር ባህል ልማድ ሀገር በቀል እውቀት በሰብዓዊነት መንገድ አንዱን ወገን ተሌላው ወገን ያገናኝ እንደነበረም ምስክርነት ይሰጣል፡ ፡ በኢትዮጵያ ጎሣዎች መካከል የነበረውን የመንፈሳዊ ባህል መወራረስና ውኅደትንም እናስተውላለን።

የሀገር ሰላም ሲታወክ በየትኛውም አጋጣሚ ልዩነት አልነበረም፤ አይታሰብምም (ቃል መረጃ ሰጪ፣ ባዩህ በዛብህ፣ አሰበ ነጋሽ)። ይህን ጉዳይ የሚከተለው የሀገር ቤት ግጥም ደህና አድረጎ የሚገልጠው ይመስለኛል፤

> . . . . . . .ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራችን፣
> ይህ ነበር መመሪያው የኢትዮጵያ ሀገራችን።
> (ሼህ ሰይድ፤ 12/11/2015 ዓ.ም. ቆላድባ)

እንዲሉ፣ ለምሳሌ፤ ጠሃር አብደላ የተሰኙ ግለሰብ በጻፉት ማመልከቻ፣ "ለጠላት መሣሪያ ሳልሆን እንደ ሀገሬ ሰው ሁሉ አርብ ገበያ ጋይንት ላርበኞች ጥይት እየሰጠሁ ሀገሬን አገለግያለሁ። . . . . በሂደት ተጀግኖቹ ተቀላቅየ በጫካ በዱር በአርበኝነት አገለግያለሁ። በጥላት እጅ ቆስያለሁ። ዋጋየን አላገኘሁም። ጠላት ሠርቶ ጥሎት ከሄደው ቤት በሽልማት ይሰጠኝ. . . ." (ጎክ/29 ዶሴ ቁጥር 29/ሸሚዝ ቁ/9/ ተ.ቁ.16 1950 ዓ.ም.)።

ልክ ጣሊያን ከሀገር እንደወጣ ንጉሠ ነገሥቱ እንደተመለሱና ከዙፋናቸው እንደተቀመጡ የጥላት ንብረት ጠባቂ የተባለ ተቋም ተቋቁሞ ስለነበር ጎንደር ላይ የነበረው በጠላት የተሠራው ቤት ንብረት እንዲህ ቀላል አልነበረም። ጎንደር ከተማ ላይ እስካሁን የሚታዩት በርካታ ቤቶች ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ተጠቃሹ አርበኛ ልክ እንደሌሎች ዋጋችንን አላገኘንም እንደሚሉት አቤቱታ አቅራቢ አርበኞች ጉዳዩን ማቀረቡን እንረዳለን። ከዚህ ላይ የመተባበርና የሀገር ስሜቱ ነገር ምንም እንኳን ጣሊያን የቅኝ ግዛት ዓላማውን ለማሳካት በሃይማኖት የመከፋፈል ዓላማ ይዞ ቢነሳም እንዳልተሳካለት የአርበኛ ጠሃር አብደላ ሥራ እንደአብነት የሚያስረዳን ነው። ከዚሁ ሳንወጣ የአርበኝነት ሥራን አስመስክሮ ለተለያየ የሥራ ዘርፍ መወዳደር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሚስተዋል ነው። ለደብረ ታቦር አውራጃ ናኢባ ፍርድ ቤት ዳኛ የተወዳደሩት ግራዝማች ሼህ ደሴ አስፋው የተመረጡበት መንገድ ከሃይማኖት እውቀታቸው በተጨማሪ በአምስት ዓመቱ የጠላት አስተዳደር ጊዜ አርበኝነት ሙያ ስለሠሩ ነበር (ማመልከቻ ጥር፣ 1949 ዓ.ም.)። ቀኛዝማች ይማም ገበያው የተባሉት እምነታቸው እስልምና የሆነ አርበኛ እንዲሁ በደብረታቦር አውራጃ ግዛት በነጭ ለባሽ መሥሪያ ቤት ምስክሮች ድምፅ እንደተገለፀው፣ " . . . .ለመንግሥታቸውና ለውድ ሀገራቸው በአርበኝነት ብዙ የደከሙና ያገለገሉ መሆናቸው የታወቀ ነው. . ."ይላል (ማ/ጎ/ዞ/መ/ክ/ ቃል ጉባዔ፣ 1946ዓ.ም.)። እዚህ ላይ ምስክርነቱ ውለታቸው ከግምት እንዲገባ ሆኖ የሚመጥን ሥራ እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው ክፍል መረጃ ለመስጠት ነበር። ይህም የትብብርንና ያንድነትን መንገድ ከፍ አድርጎ የሚያሳየንና የሚያስተምረን ጭምር ነው። ቀኛዝማች ይማም በጋይንት አውራጃና በጠቅላይ ግዛቱም በተለይ በቃዲ ፍርድ ቤት ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ስለመሆናቸው ምስክርነት የሚሰጡ በርካታ ሰነዶችና የቃል መረጃዎችም አሉ።

በ1956 ዓ.ም. የሶማሌን ሪፐብሊክ መንግሥት መመሥረት ተከትሎ የታላቋ ሶማሊያ አቀንቃኖች በድንበር አካባቢ የሚያደርጉትን ትንኮሳ በማስመልከት የሊቦ አውራጃ አስተዳደር በወቅቱ ለሀገር ግዛት ሚኒስቴር የጻፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል፤

> . . .ገጠር ከተማ ነዋሪው ሕዝባችን ክርስቲያን እስላም ወንድ ሴት ያለመለያየት ሁሉም ባንድ ላይ የካቲት ፯ ፱፻፶፮ ባውራጃው ግዛት ጽ/ቤት በመሰባሰብ ለሀገር ፍቅር ያለውን ገልጧል። ከሁለት ሽህ ያላነሰ ሰው ተገኝቶ በቆራጥነት የተነሣና የተደራጀ መሆኑን በመግለጽ....እየተነሣ እንቅስቃሴውን በፋከራና በሽለላ ይገልጽ ነበር......።

5 ጥንታዊት ጎንደር ከተማ አንድ ክፍል አዲስ ዓለም።

(የሊቦ አውራጃ ጽ/ቤት ለክቡር የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ገዥ የደብዳቤ ቁጥር 1601/12//ተ56 ቀን የካቲት ፺/፶፺ ዓ.ም.)።

በተጨማሪም በግጥም መልክ፤ “አላየሁም አልሰማሁም ብላ ሕዝብዎን ስትወቅሰው፤ ይላኩን ግርማሆይ እጃችን ትቅመሰው” የሚል የሀገር ፍቅር ቀስቃሽ ባህል የሚገልጽ  የማበረታቻ ግጥምም በጽሑፉ ወስጥ ተካቶ  ይገኛል።

ይህም ሁኔታ ከመንግሥት እስከ ታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል የነበረውን የመተባበር መንገድ የሚያሳየን ነው። ጋን በጠጠር ይደገፋል እንዲሉ ትንሽ ትልቅ ሳይባል እከሌ ነጋዴ ነውና ወይም ገበሬ፣ ብረት ሠሪ፣ አዝማሪ  ስለሆነ ወይም ሃይማኖቱ እስላምና ወይም ክርስትና አለዚያም አይሁድ ስለሆነ ለሀገር ጉዳይ አያገባውም እንዳልተባለ የሚያሳየን ነው (ቃለመጠይቅ፤ አቶ ሽመልስ ደምለው፤አቶ ባዩህ በዛብህ)። ይህም የኢትዮጵያን ሆደ ሰፊነት የሚያሳየን ነው።

ባህላዊና ማኅበራዊ ግንኙነቶችንም ስናይ መለኪያቸው ለማኅበረሰቡ መልካም እሴት ተገዥነት (ሰብዓዊነት) ሰውነትን ማስቀደም ላይ ያተኮሩ ነበር። ፍትሕ ሲጓደል ሰው ሲበደል እንስሳትም ሲበደሉ ዝም የሚባልበት ዘመን አልነበረም (ባዩህ በዛብህ፣ አባ ጌጤ አለሙ፣ አሰበ ነጋሽ)።  አማይነት (ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊሙ) የእምነት አስተምሮቶቹን በተግባር ማሳየት፣ ርኅራሄ፣ መተባበር፣ ፍትሐዊነት፣ ታማኝነት፣ ቃልኪዳን መጠበቅ፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ እውነተኝነት፣ ይሉንተኛነትን መጥቀስ ይቻላል።  በእነዚህ እሴቶች ይተዳደራል፤ ይመራል፤ የጋራ ስለሆኑ ሁሉንም ማኅበረሰብ ያለምንም መለያየት ይቆጣጠሩታል። ለዚህም ነው “እሴቶች የአንድ ማኅበረሰብ  የጎልውና ዋስትና ናቸው” የሚባለው (ባይለየኝ፣ 2011ዓ.ም.፡145)። እዚህ ላይ የክቡር ራስ አሞራው ውብነህ ተሰማ በንጉሥ ችሎት ላይ የሠሩት ሥራ ይህን የጥናቱን አካባቢ ባህል የሚነግረን ይመስለኛል። ስመጥሩ አርበኛ ራስ አሞራው ውብነህ ተሰማ (አባ ዘልስ) በሕግ መወሰኛ ምክርቤት በነበሩበት ጊዜ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ ጋር በንጉሥ ችሎት ተቀምጠው ሼህ ሙዘሚል የተሰኙ የወሊሶ ሀገር ሰው ዋስ የሚሆነኝ አዲስ አበባ የማውቀው የለኝም ብለው ሲቸገሩ ባዩ ጊዜ እኔ እዋስሃለሁ፤ ከቤቴም ተቀምጠህ ነገርክን አብረን እንከታተላለን ባሉ ጊዜ ንጉሡ “የማታውቀውን ሰው!” ብሎው ሲናገሯቸው “ላመንኩበት ነገር ራሴ እወጣዋለሁ” በማለት ዋስም ሁነዋቸው ከቤታቸው በመውሰድ አንድ ዓመት ተኩል የቤት ዕቃ አሟልተው አኑረዋቸዋል፡፡ የሼህ ሙዘሚል ባለቤትም ከሀገር ቤት መጥተው አብረው እንዲኖሩ ተደርጎ ሴት ልጅ ለመውለድም በቅተው ስሟን “ጎንደር” ብለዋታል...። የልጂቱ ስም ራስ አሞራው ጎንደሬ ስለሆኑ ውለታቸውን ለመዘከርና የጎንደርን ሰው ባህል ለማስታወስ ለማክበር ይመስላል። በኋላም ሼህ ሙዘሚልም በፍርድ ረተው በነጻ ተፈትተው ጉዳያቸውን ቋጩ። የሁለቱ ግለሰቦች ዝምድና ለልጅ ልጅ ደርሷል (ቃለመጠይቅ፣ አራጋው ገበየሁ፤ ኢትዮጵያ፣ ፲፱፻፲፱ ዓ.ም፡ ፲፱፻፳ -፳ ይመልከቱ)።

ሙስሊም ክርስቲያኑ በእቁብ፣ በእድሩም አይለያይም። በንግዱ ዓለም ሳይቀር በሽርክናም አብሮ ይሠራል (ባዩህ በዛብህ፣ አባ ጌጤ አለሙ፣ አህመድ ሙሃመድ)። በዐቢይ ፆም ሙስሊም ሠርግ አያደርግም፤ አይድርም፤ በረመዳንም ጊዜ ክርስቲያን ልጁን አይድርም፤ ሌላም ይህን የመሰለ የማኅበራዊ መድረክ አያደርግም ከማን ጋር ልደሰት? ልጄን ማን ሊመርቅልኝ? ያለ ወገኖቼ ደስታ የለኝም፤ አልበላም፤ አልጠጣም፤ በሚል ሐሳብ ሁለቱም የእምነት ተከታዮች አንዱ ያላንዱ ሠርግ አያደርግም ነበር (ዝኒከማሁ)፡፡”...ሃያልነው ውዴታ የአምላክ በረከት፣ ረሕመት የሚያወርድ በላ እሚመክት...”እንዲሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ  እንደ አቶ ባዩህ አነጋገር ማንም አስገድዶት ሳይሆን አብሮ መኖርና መተሳሰብ ያመጣው የፍቅር መንገድ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት እሴቶች የሚያሳዩት መትከያና ማሳያ ማኅበራዊ ተቋማትም ነበሩ። ለምሳሌ፤ የጡት ልጅ/ አበልጅ፣ የፈውስ / የፀበል/ ቦታዎችን በጋራ መጠቀም እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

የጡት ልጅ/አበልጅ/ በሁለት በሥጋ ባዕድ በሆኑ ግለሰቦች መካከል ዝምድናን ለማጠንከር፣ ሁሉም አንድነትን ለመትከል ሲባል የሚፈጸም አንዱ የአብሮነት ተቋም ነው። አበልጅ በሙስሊሞችና ክርስትያኖች መካከል ይከሔዳል። አንድ ሙስሊም እናት የክርስቲያን ወዳጇን ልጅ ታቅፋለች፤ በእምነቷም ቃልኪዳን ትገባለች። ዓላማውም እንደተባለው ዝምድና፣ መከባበርና ፍቅር ነው፡፡ ፍቅርም የሰብዓዊነት ጥግ የአምላክ ቃል ነው። ለሥጋ ልጅ የሚደርገው እንክብካቤ ለጡት ልጅም አይለየውም። የቃልኪዳን ነገር ስለሆነ በሁለቱም  አማኞች በጥብቅ የሚከበርና የሚተገበርም ነው። ዓላማውም እንደተባለው ዝምድና፣ መከባበር መተሳሰብ ነው (ፍሬሕይወት፣እ.ኤ.አ.፣2018፡82-85)። ደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃልም ይህንኑ ያረጋግጣል (ደስታ፣ 1962ዓ.ም.)።

ባህላዊ ክዋኔዎች ስማቸው አንድ መስሎ ከቦታ ቦታ በተግባር ላይ ሊለያዩ ይችላሉ። የጡት ልጅ በአንዳንድ አካባቢዎች በስጋ ባዕድ በሆኑ ሁለት ግለሰቦች መካከል በኑሮ ለመጠቃቀም፣ ለመረዳዳትና ዝምድናን ለመቀጠል የሚፈፀም አንድ ባህላዊ የአብሮነት እሴት ተቋም ነው። ይህም የቃልኪዳን ዝምድና ከስጋ ዝምድና እንደሚበልጥና እንደሚከበር ከትውልድ ትውልድ እየተሻገረ ከስጋ ዘመድ ማይለይ ነው። ከእምነት ጋር ባብዛኛው እንደማይገናኝ ከመረጃ ሰጪዎቼ ተረድቻለሁ (ቃለመጠይቅ ከወርቁ ገሰሰ ጋር፣

13/4/2007 ዓ.ም.)።

ሆኖም ግን ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ የጡት ልጅንና አበልጅን የመደበላለቅ ሁኔታዎች አሉ። ምንም እንኳን ሁለቱም ይሁንታ ሊቸራቸው የሚገቡ መልካም የባህል እሴቶች ቢሆኑም ዝምድናንና መከባበርን አለመከዳዳትን፣ የፍቅርንና የመተሳሰብ መግለጫ ቢሆኑም እንደ አብዛኛው ሰው እይታ አንዱ እምነታዊ ሲሆን፣ ሌላው ዓለማዊ ዝምድናን ይይዛል። ለምሳሌ፤ አበልጅ /የክርስትና ልጅ/ እምነት ጋር ይያያዛል። ነገርግን አበልጅ ሃይማኖታዊ አይደለም የሚሉ ከነምክንያታቸው ያስረዳሉ (አባ ጌጤ አለሙ፣ አቶ አሰበ ነጋሽ)። ሰው እምነቱን ጠብቆ ዝምድናውን የሚያጠብቅበት ተቋም ነው። የጡት ልጅም ቢሆን ከዚህ የተለየ ዓላማ የለውም፡፡ ዝምድናን ፍቅርን ማጠንከር ሰብዓዊነትን ለፈጣሪ መታመንን ማረጋገጫ ከባድ ማኅበረሰባዊ፣ ሀገራዊ ኃላፊነትን የመሸከም ጉዳይ ነው። ሰው ባይተዋርነትም እንዳይሰማው ወደ ማኅበረሰቡ መቀላቀያ መዘነቂያም መንገድ ሊሆን ይችላል። በርካታ ማኅበራዊና ባህላዊ መልዕክት አለው። ኅብረተሰብን አሰናስሎ፣ አስተሳስሮ አፋቅሮ የሚያኖር ሁነኛ መንገድ ነበር።

ለምሳሌ፤ እማሆይ ራዱ ብዙነህ የ90 ዓመት አዛውንት ሲሆኑ፣ የሕይወት ተሞክሯቸውን በሚከተለው መልኩ ነግረውኛል። እማሆይ የሚኖሩት ጎንደር ከተማ በተለምዶ አውቶ ፓርኮ እየተባለ ከሚጠራው ሰፈር ነው። ውልዳቸውና እድገታቸው ግን ጭልጋ ወረዳ ውስጥ አውራርዳ ቀበሌ ነበር። ስለጡት እናታቸው ሲያወሩ ስሜታዊ ከመሆናቸው የተነሣ እንባቸው ይመጣል። የእማሆይ የጡት እናት ሐዋ አብዱ ይባሉ እንደነበርና እኚሁ እናት የሰጧቸው የማጫ ላም እንደነበረችና አሁንም በዐይነ ኅሊናየ ትመጣብኛለች ይላሉ። እንደ እማሆይ አገላለጽ ከወላጅ አባታቸው ቤት ከነበረው የቀንድ ከብት መንጋ፣ የፍየልና ሌሎችም እንስሳት ይልቅ የላሚቷና ጥጆቿ ነገር ለርሳቸው ልዩ ነበር ይላሉ። ከአባታቸው ከወላጅ እናታቸው ቤት ካለው ማርና ቅቤ፣ እንዲሁም እንክብካቤ ይልቅ የጡት እናታቸው ትበልጥብኝ ነበር ይላሉ። እስካሁንም ድረስ ከጡት እናታቸው ልጆችና የልጅ ልጆች ጋር እንደሚጠያየቁ አጫውተውኛል (እማሆይ ራዱ፣ 23/ 3/2014 ዓ.ም.)

ሌላው አቶ ባዩህ በዛብህም እንዲሁ የወዳጃቸውን ልጅ በጡት አባትነት እንዳቀፉ ይናገራሉ፤ የታቀፈው ልጅ በአባቱ የመናዊ፣ በእናቱ ደግሞ ጎንደሬ ሲሆን፣ አቶ ባዩህ ልጁን እንደ ልጃቸው አድርገው ሊያዩት ቃል እንደገቡ ይናገራሉ። እስከቅርብ ጊዜም ድረስ ከቤተሰቡ ጋር እንደሚጠያየቁ፣ ልጁም በየመን አየር ኀይል ውስጥ ይሠራ እንደ ነበር፣ አባቱም ጎንደርን ይወድ ስለነበር ከብዙ ጊዜያት በኋላ ከሚኖርበት ሀገር መጥቶ ጎንደርን ጎብኝቶ እንደተመለሰ ነግረውኛል (ቃለመጠይቅ ከአቶ ባዩህ በዛብህ፣ 5/3/15ዓ.ም.)፡፡ እዚህ ላይ ይህ ያብሮነት ባህል እስከ ባህር ማዶ ድረስም ኢትዮጵያዊያንን ከጎረቤት ሀገራት ዜጎች ጋር አዛምዷል ለማለትም ያስደፍራል።

በሀገራችን ባህል በደስታም ሆነ በመከራ ከጎረቤት፣ ወዳጅ ዘመድ ጋር አብሮ ማሳለፍ ጥልቅ ልማድ መሆኑ የታወቀ ነው። በተለይ በደስታ ጊዜ ለሚወዱት ሚዜ ጋሻ አጃግሬ መሆን የተለመደ ባህል ነበር። የመዛመጃ አንዱ መንገድ ስለሆነም ሚዜን የሚመርጡ ወላጆች ነበሩ። ልጅህ ለልጄ ሚዜ ይሁነው ተብሎ ለማለት ነው። ለዚህም ጉዳይ ሽማግሌ ይላካል። አቶ ምንተስኖት በጎንደር ከተማ ተወልደው ያደጉ ናቸው። አባታቸው ቄስ አቡሃይ ይባላሉ። ቄስ አቡሃይ በርካታ ወዳጅ ዘመዶች ስለነበሯቸውና አቶ ምንተስኖትም በዚሁ መስተጋብር እንዳደጉ ይናገራሉ። በ1963ዓ.ም. ለትዳርና ወግ ማዕረግ ሲበቁ የስር ሚዜዎቻቸው ዐሊ ደጉና ዐሊ የሱፍ የሚባሉ ሙስሊሞች እንደነበሩ፣ እንዲሁም ጨፍረውና ዘፍነው እንደዳሯቸው ከግራ ቀኝ ተመርቀው ሙሉ ሆነው እንደኖሩ አጫውተውኛል። በተጨማሪም፤

> ....አባታችን ቄስ አቡሃይ ገ/ሥላሴ ከሐጅ መሃመድ አብደላ ጋር የቅርብ የሥጋ ዘመዳሞች ናቸው። የፍቅራቸውና የመተሳሰባቸው ነገር የሚገርም ነበር። ለውሏቸውና ለአዳራቸው አይተማመኑም ነበር። አንደኛው የአንደኛውን እምነት የሚያከብሩበት መንገድና ጥንቃቄ እጅግ በጣም ልዩ ነበር....። ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ቀን ሐጅ መሃመድ ከቤት ቢጠፉ ቄስ አቡሃይ ወደ አዲስ ዓለም መኖሪያ ቤታቸው ሊፈልጋቸው ሲሔድ መንገድ ላይ ሙስሊሞች ተሰባበስበው በሬ አርደው ቅርጫ ሲከፋፈሉ ይደርሳል። የኔ ወንድም ከዚህ ቅርጫ አለበት? ብሎ ሲጠይቅ፣ ማነው? ሲሉት ሐጅ መሃመድ አብደላ ይላቸዋል። እርሱ የለበትም የሚል ምላሽ ይሰጡታል፤ ቄስ አቡሃይም በሉ አንድ መደብ ያዙለት ብሎ ዋጋውን ከፍሎ አሸክሞ ሐጅ መሐመድ ቤት ሄደ። ከዚያም በተረብ (ቀልድ) ቅርጫ ገብቼ ስለነበር ይዤልህ መጣሁ ብሎ ለሐጅ ሲነግራቸው፣ አንተስ ታደርጋለህ .....! ባሉት ጊዜ እዚህ ማዶ ሙስሊሞች በሬ አርደው ሲከፋፈሉ አግኝቼ አንድ መደብ ይዤልህ መጣሁ ይላቸዋል። ሐጅም አዬ! ወንድሜ ብለው እየተተራረቡ ስጋውን ተቀበሉ፤ በቤቱም ሳቅ ጨዋታ ደስታ ሆነ በማለት አጫውተውኛል (ምንተስኖት፣ ቃለመጠይቅ 23/1/16ዓ.ም.)።

በሠርግ ጊዜ ሚዜ ከመሆን በተጨማሪ አንዱ ላንዱ ዋስ ጠበቃም እየሆነም ይኖር ነበር። ችግር ባጋጠመም ጊዜ መረዳዳትና መተጋገዝ የተለመደ ነው።..ለምሳሌ፤ ኑሬ ሐሰን የተባሉ ግለሰብ አይከል ናራ ጭልጋ ከባላምባራስ ሰማ እንግዳ 500 መቶ ብር ሲበደሩ እንዳገሩ ልማድ ዋስ የጠሯቸው ሰዎች የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑትን ወ/ሮ ማንጠግቦሽ በቀለንና ብላታ ይመር

መሸሻን ነበር (ጎንደር ፋይል ቁጥር 12547/29/50 ቀን 18/8/50ዓ.ም) ።

ይህን የአብሮነት ልማድ የሚቀጥለው ያንድ አባት "ታሪክን በቅኔ" ትዝብት የበለጠ ስለሚገልጠው የተወሰነውን ወስጀዋለሁ።

…አገር ቤት ስንኖር አብረን በገጠር
መጋጨት አናውቅም በእርሻ በድንበር. .
ዝምድና ጨምረን አበልጅ ሁነን
እምብዛም አናቀው የሚለየንን . . .
ሚዜ ጋሻ ጃግሬ ሚስጥረኞች ነን
ዘፈን ጭፈራውን ሁሉንም አብረን
በሠርግ ባውዳመቱ አብረን ተባብረን
ፀሎት አይለያየን ምርቃታችን…. .
(ሼህ ሰይድ ኢብራሒም ቃለመጠይቅ 12/11/15 ዓ.ም.ቆላድባ)

ይህ ግጥም በፍቅር የመኖርን ዘይቤ የሚያስዳስሰን ሲሆን፣ እዚህ ላይ ይነስም ይብዛም ልዩነቶች የሉም ለማለት ሳይሆን ክርስቲያኑና እስላሙ ተግባብቶና ተሳስቦ በሚለየው ተለይቶ በሚያቀራረበው ተቀራርቦ አብሮ ይኖር እንደነበር የሚሳየን ነው። ተግባብተን፣ ተጠባብቀንና ተሳስበን እንኖር ነበር ለማለት ጭምር ነው (ሼህ ሰይድ ኢብራሒም፤ ባዩህ በዛብህ፣ ጌጡ ዓለሙ)።

በሁለቱ አማኞች መካከል ዝምድና ፍቅርን የበለጠ የሚተክሉ ማኅበራዊ ተቋማትንም በግጥሙ ውስጥ ለመግለጽ ተሞክሯል። በፍቅር ሃይማኖታዊ ባዕላትን ማክበር፣ በልዩነት አብሮ መብላት መጠጣት፣ በደስታ፣ በሐዘን በመከራ መጠያየቅ የነበረና ያለ ነው። ለምሳሌ፤ ጥምቀትን፣ ፋሲካን፣ መስቀልን፣ ገናን፣ መውሊድን፣ ፈጥርን፣ አረፋን የመሳሰሉትን በዓላት አብሮ ያከብራል። እንኳን አደረሳችሁ እንኳን አብሮ አደረሰን የከርሞ ሰው ቀለብ የማያነሰው ይበለን! በመባባል መተሳሰቡን በግብር ይገልጻል።

ቅዱስ ቦታዎችንም ማክበር የሁለቱም አማኞች ጠባይ ነበር። ቅዱስ ቦታዎች ስንል አብያተክርስቲያናነት፣ ገዳማት፣ ውጅብ / መስጅድ፣ የፀበል/ዘምዘም ውሃ፣ የመቃብር ቦታዎችን፣ የታላላቅ ሰዎች ዱዓ ያደርጉባቸው የነበሩ ቦታዎችን ይመለከታል።
ሲጠሩ እንኳን "አባዬ ልጅ አሞብኝ እራሱ እየቆሰለ፣ እያንቀጠቀጠው. . . ." እየተባለ ጉዳዩ የሚነግሯቸው አባቶች የሀገር መድኃኒቶች የዓይን፣ የጀሮ፣ የሆድ፣ ሌላም ይህን የመሰለ ባላቸው በተሰጣቸው ፈልገውም ባገኙት እውቀት የሚያድኑ ሀገር የሚያስታርቁ፣ መከራን ቸነፈርን ተፈጣሪያቸው ጋር ተነጋግረው በጸሎት የሚይዙ ተብለው የሚታመንባቸውን አባቶችን ለማለት ነው፡፡ በመቃብር ቦታ ሲታለፍ አሁን ድረስ ክርስቲያን እስላም ሳይባል መኳንት ቢሉ ተራ ሰው ተበቀሎው ወርዶ ባርኔጣውንም ተራሱ ላይ በማክበር በማውረድ ነው የሚታለፈው። በሁሉም የመቃብር ቦታዎች በክብር የሚጠበቁ ነበሩ። በተለይ የሀገር አባት በሚባሉ ወልዮች አካባቢ እንጨት አይቆረጥም ይከበራል (አስማማው፣ 2015 ዓ.ም፣ አሰበ ነጋሽ፣ አባ ጌጡ አለሙ)
ቅዱስ ቦታን በመንብኘት ረገድ "ጥርት" ባለው የእምነት መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ወደ አንዱ የጸሎት ቦታ ወይም መውሊድና ክርስትና ሂድ የሚል ትዕዛዝ ላይኖር ይችላል። ይሁን እንጂ ስለፍቅር፣ ስለጉርብትና ሐቅ ያስተምራል። ሃይማኖተኛ ነው/ናት የሚለው ባህላዊ አስተሳሰብ በማኅበረሰቡ የያዘው ቀኖና ሲታይ ለባህልና ለማኅበረሰብ መልካም እሴት ተገዥነትን የሚያሳይ እንጂ እምነቱ ክርስቲያን ወይም እስላም መሆን አይደለም። ሃይማኖተኛ በአካባቢው እሳቤ ቅንነት፣ ታማኝነት፣ አስተዋይነት፣ አርዓያነት፣ አብሮ መብላት፣ ግብረገብነት፣ ሐቅን ማወቅ፣ የአብሮ መኖር ቱሩፋቶችን ለይቶ ማወቅ፣ ትልቅን ማክበር፣ ምርቃትንና እርግማንን የመለየት አቅም፣ ሰብዓዊነትንና የመሳሰሉትን እሴቶች ይይዛል።

የጸበል/ዘምዘም ውሃ ቅዱስ ቦታዎች በተመለከተ በየትኛውም እምነት ስር ቢሆኑም ማንኛውም እምነት ተከታይ ጸበሉን ወስዶ የመጠቀም መብቱ የተከበረ ነው። ባይሆን እንደየ ሁኔታው ጸበሉን የሚቀዳ ሰው ሊያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር። በዋንዛዬ፣ በባታ፣ በሼህ አባድር፣ በሼህ አብዱልባሲጥ ዘምዘምና ጸበል ያለውን እውነታ መጥቀስ ይቻላል።

ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የክርስትና የእስልምና እምነት ተከታዮች አያቶቻቸው በየእምነታቸው ባርከው ስጋውን አብረው ባንድ ማሰሮ አብስለው እንዳይጠፋቸው ምልክት አድርገው አውጥተው የየራሳቸውን ይመገቡ እንደነበር አስረድተውኛል (እማሆይ በለጡ ሻረው፤ በያን ገበያው 12/3/2005 ዓ.ም.)። ይህም በባህል እሴት የተሳሰረው የፍቅራቸውን ልህቀት ያሳየናል። በጸሎት አንረሳሳ የሚለው ባህላዊ እሴትም የእምነት እኩልነትንና አብሮነትን መከባባርን የሚሳይ ነው። ጸሎትህ ደረሰኝ፤ ጸሎትሽ ደረሰኝ መባባልም የተለመደ እንደሆነ መገንዘብ ያሻል።

...ጀግናው ጎንደሬ ብሎ ጀማሪ፣
እስላም ታማራ6 አክብሮ አዳሪ
አየ ዓለም ፈራሽ አየ አለም ቀሪ፣
የድሃው ባላ የውሩ መሪ

አገሩን ወዳድ ወገኑን አኩሪ.... ። እንዲሉ (አብረሃም ድልነሳ፣ 12/12/15ዓ.ም)

ሲመረቅም፤ "የሰላም ያማራውን፣ የወፍ ያሞራውን ሃጃ[7] አላህ ያውጣው!" ይባላል (ሼህ መሐመድ ኢብራሒም ገደብየ መስመር ሸንበቂት 12/7/15 ዓ.ም.)።

"ይህ ነው ያደግንበት ታሪካችን አብረን ታቦት አውጥተን ዘፍነን አስገብተን ተመራርቀን ነው ያደግነው። በደብርና ትልልቅ የሀገር አባት ሼኮች የሀገር ጸሎት አድራጊዎች መቃብር ሲታለፍ ከበቅሎ ተውርዶ ነው፤ ምን የተሾመ የተሸለመ ቢሆን ያከብራል፤ እስላም ክርስቲያን አይልም፤" (ቃለመጠይቅ፤ ባዩህ በዛብህ፣ 2/3/16ዓ.ም)። እንደተባለው "የግጥሙ መልዕክት እጅግ ጥልቅ ይመስላል፤ ለተመለከተው ላስተዋለው ሰው" እንዲሉ የሚያሳየን ገጣሚው በጥበብ ያደጉበትን የትብብርንና የመግባባት ሰብዓዊነት የሞላው የተኖረ መከባበር አብሮነት በዓይነ ኅሊና እንዳስመለከቱን ለመገንዘብ የሚያዳግት አይመስልም። ቤተክርስቲያንም ሆነ መስጅድ አብሮ ተረዳድቶ መሠራት የተለመደ ያብሮነት መገለጫም ነው። ይህ የመልካም ጉርብትና መገለጫ ነገር አሁንም በብዙ ቦታዎች ይስተዋላል። አፄ ፋሲል በዘመነ መንግሥታቸው ከተከሏቸው አብያተክርስቲያናት አንዱ የሆነውና በ1623 ዓ.ም. የተተከለው አደባባይ እየሱስ ቤተክርስቲያን እድሳት ሊደረግለት ታስቦ ሥራው ይሳለጥ ዘንድ የደርግን ባለሥልጣናትን በጎ ፈቃድ ለመጠየቅ የክፍለሀገሩ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ እንድሪያ ጥቅምት4 ቀን 1970 ዓ.ም. በቁጥር 44/70 ለክፍለሀገሩ ቋሚ የደርግ ቡድን ጽፈው ባሳሰቡት መሠረት የአሠሪው ኮሚቴ በአዘጋጀው የሥራ ደንብ ውስጥ አንቀጽ ሦስት ገጽ17 ላይ ኮሚቴው በጎሣ፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ልዩነት ሳያደርግ የእርዳታ ልግስና ትብብር እንደሚጠይቅ ያወሳል። ይህ የሚያሳየን ሲውርድ ሲዋረድ የመጣውን በልዩነት ውስጥ ያለ የትብብርና የመከባበር መንገድን ነው።

## ፫. መደምደሚያ

ጥናቱ ለመዳሰስ የሞከረው ዐቢይ ጉዳይ የእምነት አብሮንትና መከባበር በቀድሞ ጎንደር ክፍለ ሀገር አካባቢ ምን ይመስል እንደነበር መፈተሽ ነው። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በሃይማኖት ግንኙነት ታሪክ ግጭትንም ሰላማዊ ግንኙነትንም ያሳለፈች ብትሆንም በአብሮነትና በመከባበር ታሪክ ውስጥ ልዩ ቦታ ያላት መሆኑን ይህ ጥናት በትንሹም ቢሆን ምስክርነት ይሰጣል። የጥናቱ ውጤትም እንደሚያሳየው የአካባቢው ሕዝብ እንደሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ሁሉ አወንታዊና አሉታዊ ግንኙነቶችን በማለፍ አማኞች ክርስትናንም ሆነ እስልምናን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በተለይ በተራው ማኅበረሰብ መካከል ልዩነቱን አክብሮ በፍቅር አብሮ የመኖር እሴቶችን እያዳበሩ እንደመጡ ለማየት ተሞክሯል። ሁለቱም አማኝ ወገኖች በጋራ የማኅበራዊ ሕግጋት እንደነበራቸው መታዘብ ይቻላል። እነዚህ በሕዝቡ ውስጥ ያሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ለጋራና በጋራ አብሮ ለመኖርና ለሰብዓዊነት እንዲያግዙ ተደርገው የተሠሩ ናቸው። ጥናቱ እነዚህ በዘመን ብዛት ዳብረው የሚስተዋሉ እሴቶችን መጠበቅና ማስተማር ብሎም ለትውልድ ማስተላለፍ ጠቀሜታ እንዳለው ምክረሐሳብ አለው።

ከባለፈውም፣ አሁን ካለንበትም ጭምሮ ትምህርት ተወስዶ በጎብር የተሻለ ነገር መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ ከጥናቱ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህም ጥናቱ "ታሪካችንን ታሪካችን፣ ባህላችንንም እንዲሁ ባህላችን" ማድረግ እንደሚጠቅም አመላካች ሐሳብ አለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በክፉ፣ በደጉ አብሮ ተመሳጥሮ፣ ተሰናስሎ፣ ተዋስቦ ያሳለፈው ታሪክ የሚያኮራ እንጂ የሚያሳፍር አለመሆኑን ጭምር መረዳት ያሻል። ጠቅለል ብሎ ሲታይ የአብሮነት እሴቶቻችን በእምነትም ይሁን በጎሣ የሚያሳዩን ስብጥርን፣ መስተጋብርን፣ ዝምድናን፣ አንዱ ለሌላው ድራቡ፣ ልብሱ፣ ጌጡ መሆኑን እጣፈንታውም አብሮ የተወሰነ መሆኑን ነው። የጎንደር አካባቢ የሃይማኖት መከባበር ታሪክ በጎብር ያማረ አንድነትን የሚያሳይ ነው። ይህም እንደ ትልቅ ጸጋ ሊቆጠር የሚገባው ይመስላል። "....እኛ ኢትዮጵያዊያን ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ቋንቋዎች ያሉን እንጂ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች ምክንያት የተለያየን አይደለንም" እንዲሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሀገራችን ሰው ሲናገር፣ "አለ ብዙ ነገር የምንማረው፣ ብናይ ወደ ኋላ ብንመረምረው" የሚለው ፈሊጥ ትኩረትን የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል።

---

6 አማራ የሚለው በተለምዶ ለኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ክርስቲያን አማኝ እንደመጠሪያ የሚያገለግል ቢሆንም፤ የጎሣ ስምም ስለሆነ ሙስሊሞችንም ክርስቲያኖቸንም የሚያካትት ነው፡፡ ለምሳሌ፤ አንድ ሰው ዘሬ አማራ ሃይማኖቴ እስላም፣ ዘሬ አማራ ሃይማኖቴ ተዋኅዶ የሚሉ በርካታ መዛግብት አጥኝው በመስክ ሥራው አግኝቷል፡፡ ሃይማኖቴ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ወይም እስላም ይሉና ዘሬ፣ ኢትዮጵያ የሚልም በስፋት ይገኛል፡፡ የጎሣ ልዩነት ያለ ቢሆንም ጉዳዩን ጣሊያን በልዩ ሁኔታ ላገዛዝ እንዲያመቸው የተከለው ይመስላል።

7 ጉዳይውን ሐሳቡን ይፈጸምለት

## ፱. ዋቢ ጽሑፎች

የማ/እ/ ጎንደር አስተዳደር መዛግብት ክፍል፣ የሊቦ አውራጃ ጽ/ቤት ለክቡር ሌ/ጀነገራል ነጋ ተገኘ የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ገዥ ጉዳዩ ፡-የሶማሌ ሪፐብሊክ መንግሥትን መተመለከተ የደብዳቤ ቁጥርና ቀን የካቲት 1601/12//56

ማ/ጎንደር መዛግብት ክፍል፣ በጎንደር የቆመው የጀግኖች ማኅበር አባላት ለክቡር እመ ክቡራን ደጃዝማች አሥራተ ካሣ የቤጌምደር ገዥ የስሜን እንደራሴ ደብዳቤ ቁጥር የለውም ቀን ፴/ ፲፱፴፯ ዓ.ም የጻፉት ደብዳቤ።

ማ/ጎንደር መዛግንት ክፍል፣ ደጃዝማች ጣሹ እንግዳና ሽህ ለጋስ አደም የርስት ክርክር ደብዳቤ ለቤጌምደርና ስሜን ለጭቃ ይግባኝ በሥሪያ ቤት ቀን 2 1945ዓ.ም።

ማ/ጎንደር መዛግንት ክፍል፣ መዛግበት ክፍል፣ ጠሃር አብደላ ለቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት፤ ጉዳዩ፡- ውለታን ይበለከታል፣ ጎክ/ዶሴ ቁጥር 29/ሽሚዝ ቁ/9/ ተ.ቁ.16 1950 ዓ.ም.።

ኢትዮጵያ ውብነህ ተሰማ።፲፱፻፲፱ ዓ.ም። ጀግናው አርበኛ ክቡር ራስ አሞራው ውብነህ ተሰማ ፣ ሜጋ አሳታሚ ገጽ፣ ፲፻፭ -፹.

ጌታቸው ኃይሌ።2013 ዓ.ም። በግል ሕይወቴ ከደረሰውና ካጋጠመኝ አንዳፍታ ላውጋችሁ፣ ብራና አሳታሚ።

ጌታቸው ኃይሌ።2012 ዓ.ም። ከግዕዝ ሥነጽሑፍ ጋር ብዙአፍታ ቆይታ፣ገጽ፣ 413-414፣ ብራና አሳታሚ።

ጌታቸው ኃይሌ።2011ዓ.ም። “ማንነቶቻችንና መንግሥታዊ ታሪካችን” የኢትዮጵያ ተጠሪ ማነው? ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌና ሌሎች በደረጀ ይመርና ተስፋዬ ሽብሩ ( አርታኢ)።

ባይለየኝ ጣሰው።2011ዓ.ም። “የብሔራዊ ጀግኖቻችን ታሪክ እየተቦረቦረ ነው” የኢትዮጵያ ተጠሪ ማነው? ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌና ሌሎች በደረጀ ይመርና ተስፋዬ ሽብሩ ( አርታኢ)፣ገጽ፣ 145-150።

ጎይሌ ላሬቦ ። 2017።“ለመሆኑ የብሔር ብሔረሰብ ጭቆና በኢትዮጵያ ነበር ወይ? “፣ International Journal of Ethiopian Studies , Vol. 11, No. 1 & 2, Special Issue (2017), pp. 1-44.

አልማው ክፍሌ።2011ዓ.ም።”ፍትኅ የይቅርታን በር መዝጋት የለበትም” የኢትዮጵያ ተጠሪ ማነው? ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌና ሌሎች በደረጀ ይመርና ተስፋዬ ሽብሩ ( አርታኢ)፣ገጽ፣ 315-316።

አርኖሚሸል ዲአባዲ (ተርጓሚ) ገነት አየለ።2013 ዓ.ም። በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ ክፍል ሁለት ማንኩሳ አሳታሚ።

አክሊሉ ሀብቴ. (2017) .የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ታሪክ የከፍተኛ ትምህርት መቋቋምና መስፋፋት ጉዞ በኢትዮጵያ ( Taiwan Printing Press).

ኤርምያስ ሁሴን ።፲፱፻፲፮ ዓ.ም።የኢትዮጵያ ታሪክ በታደሰ ታምራት ዕይታ ጥንታዊቷና የዛሬቱ ኢትዮጵያ አሳታሚ የለም።

ውዱ ጣፈጠ:: (2004 ):: “የሃይማኖታ መቻቻል በኢትዮጵያ” ”ባህልና ልማት በኢትዮጵያ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች አርታኢ ሽፈራው በቀለ ፤ አሳታሚ ፎረም ፎር ሶሻል ስቴዲስ፤አዲስአበባ።

ፍሬህይወት ባዩ።2018። “የሃይማኖት መቻቻልን ማስተዋወቅ ለሰላማዊ አብሮነት በአርሲ ዞን ማሳያነት”፣ ዜና ልሳን Zena-Lissan፣ Volume XXVII Number 1 ።

ደስታ ተክለ ወልድ። 1962። አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ።

ደሳለኝ ብዙነህ። 2014። “የአማራ እና የቅማንት ሕዝቦች አብሮነት፣ የጋራ ድሎች እና ፈተናዎች ከታሪክ አንጻር” በሥራ ላይ ያለጽሑፍ ያልታተመ።

ኸድር ታጁ.።2012 ዓ.ኢ። ዘመነ ታሪክ ከ1863-1881ዓ.ኢ. በአበሻዳምነው የፈነጠቁ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሊቃውንት መዋእለ ሕይወትና ያርበኝነት ውሎና ድርሳናት አበርክቶ፣ ነጃሺ አሳታሚ።

*A*bdussamed A. 1989.“Derita , Begemdir : “An historic Town and its Muslim populations 1830- 1889”, *International Journal of African of African Historical Studies* , ,Vol, 22, no3 , Boston University , pp.439-451.

Abir, Mordechai. 2011. Era of princes the Challenge of Islam and the Reunification of the Christian empire 1769-1855, : Tsehay publisher.

Assefa Balcha. 2019. "Pilgrimage to Holy sites in Wallo: Past and Present ", *Journal of Afro Asiatic Langauges* , *History and Culture,* Volume 8,Number 1.

Bahru Zewde. 2001. *A Hstory of Modern Ethiopia 1855-1991*, Addis Ababa University Press.

Bahru Zewde (Edited) .2023. *Interdependence and Interactions in Ethiopian History* Friedrich-Ebert-Stiftung, Addis Ababa .

Beckingham ,C.F. and G.W.B.Huntingford. 1958. T*he Prester John of the Indies: A true relation to the lands of the Prester John being the narrative of the Portuguese embassy to Ethiopia in 1520*, Cambridge University Press, Vol. I.

Blanc,Henry . 2005. *A narrative of Captivity in Abyssinia with some account of the late Emperor Theodore his country People*, htt:// www.manbooks.org), pp.58-9

Bruce, James . 1790. *Travels to Discover the Sources of the Nile*. Vol. III. Edinburgh .

Debash Yimam. 2011. “*A history of wägära district to 1974*”. MA thesis, AAU.

Donzel,Van. . 1986.“Fasilades Foreign policy 1647-1649” . *Journal of Ethiopian Studies*, XXIX . F. Bathazer Teller, The Ttravel of the Jesuits in Ethiopia, London,1710, p.39

Dulin, John Christopher. 2016. “*Intelligible Tolerance, Ambiguous Tensions, Antagonistic Revelations: Patterns of Muslim-Christian Coexistence in Orthodox Christian Majority Ethiopia”*, dissertation Anthropology.Californina university, University of California, pp.1-291

Erlich Haggai.2013. “I*slam, Christianity, Judaism, and Ethiopia: The Messages of Religions*” , The Nehemia Levtzion Center for Islamic Studies The Institute for Asian and African Studies.The Hebrew University of Jerusalem.

Ficquet, Éloi . 2007.“*Mammadoč Dynasty*,” in Siegbert Uhli, ed., Encyclopedia Aethiopi-

ca, Vol. 3 (He-N), Wiesbaden: Harrassowitz: 2: 716

Ficquet, E. 2006. "*Flesh soaked in faith: Meat as a marker of the boundary between Christians and Muslims in Ethiopia*". In Muslim-Christian Encounters in Africa (pp. 39-56). Brill.

Ficquet, E. 2017. "*Interfaith relations between Christianity and Islam in Ethiopia" Ethiopia : History, Culture and Challenges*, in Siegbert Uhlig (etal.)edited , Michigan State University Press, pp.242-243.

Gerard Prunier and Éloi Ficquet.(editors). 2015. *Understanding Contemporary Ethiopia,* First published in the United Kingdom iC. Hurst & Co. (Publishers) Ltd.

Hussien Ahmed .1996 "Aksum in Muslim Historical Tradition". *Journal of Ethiopian Studies*, XXIX, 2.

Hussien Ahmed. 2001, *Islam in the 19th century Wallo, Ethiopia.*Leiden Brill.

Hussien Ahmed. 2006. "Co-existence and/or confrontation?:Towards reappraisal of a Christian- Muslim encounter in the comporary Ethiopia":*Journal of Rligion in Africa.*

J. poncet, Charles 1949." The Journey of Charles JacquisPoncet from Cairo in to Abyssinia and Back" in *The Red Sea and adjacent Countries: At the Close of the Seventeenth Century*, ed. W. Foster, London

J. Spencer Trimingham .1956. *Islam in Ethiopia.* London: Frank Cass & Co. Ltd., .

Leiris,Michel. 1958. *La possession et ses aspects théâtraux chez les Éthiopiens de Gondar.* Paris: Librairie Plon, 105 pp. Collection L'Homme. Cahiers d'ethnologie, de géographie et de linguistique, no 1.

Meyerson Mark D. (edit, eta). 2000. *Christians, Muslims and Jews in Early Modern Spain: Interaction and Cultural change* , University of NotereDame Press, Indiana.

Pankhurst, Richard.1996. "*Ethiopia revealed Merchants travellers and scholars*" , African Zion the sacred art of Ethiopia, Catalogue by Marilyn Heldman with Stuart C. Munro-Hay Essays by Donald E. Crummey (etal.),Yale University Press, p. 21.

Rassam Hormuzd. 1869. *Narrative of the British Mission to Theodore King of Abyssinia*, I London.

Samuel Johnson. 2007.*A voyage to Abyssinia, London:* Cassell and Company limited.

Sergew Hablessilassie.1972. Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270 Addis Ababa: United printers.

Shiferaw Bekele. 1990. "*Reflections on the Power Elite of the Wärä Seh Mäsfenate* (1786-1853)". In: Annales d'Ethiopie. Volume 15, pp. 157-179.

Solomon Addis. 1994.“A*ddis Alem: The nucleus of Gondar*” . Ethiopia in broader perspective ,V.I .

Taddesse Tamrat 1972 .*Church and State in Ethiopia*. Red Sea, Press.

Taddesse Tamrat.1988. “Process of Ethnic Interaction and Integration in Ethiopian History: The Case of the Agaw “ *The Journal of African History* , 1988, Vol. 29, No. 1, Cambridge University Press.

Teller ,F. Bathazer .1710. *The Travel of the Jesuits in Ethiopia. London. Weld,Blundell. 2007. The Royal Chronicle of Abyssinia 1*769- 1840.Cambridge : Cambridge University press and Toronto.